ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the source of the Blue Nile

# ናይል
# THE NILE



ኢ.-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

ናይል 3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 9፣ ጥቅምት 2008

## ተግባር በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)






The 14th International Symposium on Equatorial Aeronomy (ISEA) at BDU

## ገጠመኝ

አለባቸው አስፋው

## Are we really busy?

Yenus Nurie

"የምርምር አጀንዳ መሆን ያለበት በኛ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ እምቅ ተሞክሮዎችን መዝዞ አውጥቶና ሳይንሳዊ በሆነ መልክ አደራጅቶ በጥቅም ላይ ማዋል ነው።"

ዓለማየሁ ቢሻው (ዶ/ር)



ለዩኒቨርሲቲው የመጀመሪያ ዓመት ሴት ተማሪዎች የህይወት ክህሎት ስልጠና ሲሰጥ





በሂሳብና ስታቲስቲክስ ላይ ያተኮረ አለም አቀፍ ጉባዔ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሲካሄድ

## Photo Gallery

page 16

እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# ናይል THE NILE

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

**"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"**

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

### Core Values

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility


# ናይል ጋዜጣ

**በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት**
**የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል**
**የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**

**የአማካሪ ቦርድ አባላት**
ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
ዶ/ር ጥጋብ በዜ
አቶ አማረ ካሳው
አቶ በላይነህ ወርቁ
ወ/ሪት እንዳስ ቃሶ
አቶ ፈታሒ በቃሉ
አቶ ብሩክ ከተማ
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
ይናገር ተ/ስላሴ
አብነት ሰለሞን
እየሩስ ካሱ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች፡-**
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
አበባ ሐብቱ
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች፡-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ፈታሒ በቃሉ
አለባቸው አስፋው
የኑስ ኑሬ
ሸትክልት ዳኛው
ደስታ ተከስተ

**ፎቶ አንሺዎች፡-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-**
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ
ፋንታነሽ ላቀው

**ትራንስፖርት፡-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች፡-**
ንብረት ታፈረ
ይርጋ ሻረው
አለምነሽ ሙሉ

ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023

## ርዕሰ-አንቀጽ

# አብሮ የመሥራት ባህልን በማዳበር የዩኒቨርሲቲውን ራዕይ እናሳካ!

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 አፍሪካ ውስጥ ከሚገኙ አሥር የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን ራዕይ ሰንቆ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ ይህንን ራዕይ ለማሳካት የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ በማቀድ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ በሁሉም እርከን ያሉ አመራሮች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች እና ተማሪዎች እቅዱን ለማሳካት በተሰማሩበት መስክ የሚጠበቅባቸውን ሀላፊነት መወጣት እንዳለባቸው ይታመናል፡፡

‘በአንድ እጅ አጨብጭቦ በአንድ በሬ አርሶ’ የሚለው አባባል ብናስታውሰውና ለምን እንደተተረተ ብንረዳ አንዳች ትርጉም እንዳለው እንገነዘባለን፡፡ በአንድ እጅ ማጨብጨብ እና በአንድ በሬ ማረስ የማይታሰብና ሊሆን የማይችል እውነታ ነው፡፡

አንድን መሬት በደንብ ለማረስ ሁለት በሬዎች በጋራ መጠመድ ይኖርባቸዋል፤ ሞቅ ያለ ጭብጨባ ለማሰማት ሁለት እጆችን መጠቀም የግድ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ ቀደም ብለን ወደ አነሳነው ጉዳይ ስናመጣው ለብቻ ኖሮ፣ ሠርቶ፣ አድጐ ስኬታማ የሆነ የለም፡፡ ሁሉም ሥራዎቻችንና ስኬቶቻችን ከሰዎች ጋር ባለን መስተጋብርና እንቅስቃሴ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

እቅድን ከማሳካት አንፃር የተለያዩ ተግባራትን በመለየት መንቀሳቀስ ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ አብሮ መሥራት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች እና የሥራ መስኮች አብሮ የመሥራት ክህሎት እንደ አንድ የውጤት መለኪያ ተደርጐ ይቆጠራል፡፡

የአንድ ሠራተኛ፣ ተማሪ፣ መምህር ወይም አመራር ውጤታማነት በራሱ/በራሷ ጥረት፣ ፍላጐትና ቁርጠኝነት ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በዙሪያው አብረውት ከሚማሩት ወይም ከሚሰሩት ግለሰቦች ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡

አብሮ የመሥራት ባህል ለግል ስኬት ብቻ ሳይሆን ለቤተሰብና ለሀገር እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ የአንድ ግለሰብ ጥንካሬ ለሌላው መነሻ ሊሆን፣ የአንዱ ውድቀት (ውጤታማ አለመሆን) ለሌላው ትምህርት በመሆን አንዱ ከአንዱ ይዋሳል፣ ይማራል፡፡

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሰው ሀይልም ሆነ በግብአት የተጠናከሩ ናቸው፡፡ ይህን ሀብታቸውን በአግባቡና በወቅቱ መጠቀም የሚችሉት የጋራ የሆነ ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት በሚያደርጉት እንቅስቃሴና ተግባር ነው፡፡ ከተግባራቸው አንዱና ዋነኛው ለጋራ አላማ በጋራ መሥራት ነው ፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ራዕይ 2017ን ለማሳካት ቁልፉ በማህበረሰቡ እጅ ነው፡፡ በመማር ማስተማር፣ በምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሁም በቴክኖሎጂ ሽግግር የተሻለ ለውጥ ለማምጣት ማህበረሰቡ እጅ ለእጅ ተያይዞ ወደ አንድ መንገድ ማምራት ይኖርበታል - ወደ ራዕይ 2017!

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን
የተለያዩ ጹህፎች፣ ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች፣ የካርቱን ስእሎች፣ ቀልድ፣ ግጥም እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል grac-etsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

## ቁልፍ መልዕክት

# ተግባር በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

ተግባር በሚለው ሀሳብ ላይ በርካታ እይታዎች አሉ፡፡ እነዚህ ዕይታዎች እንደ ዘርፉ ያላቸው ይዘትና ጥልቀት ይለያያል፡፡ በሳይንስ ዘርፍ ተግባር የአንድን ንድፍ ሀሳብ መመዘኛ ሆኖ ይወሰዳል፡፡ በዚህም መሠረት አንድ የሳይንስ ንድፍ ሀሳብ በተግባር ከሠራ ተቀባይነት እያገኘና እየሰፋ ሲሄድ ካልሠራ ደግሞ ውድቅ ይሆናል፡፡ ሀሳቡን ማንም ያፍልቀው ማን በተግባር ካልሠራ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በህግና በስነ-አዕምሮ ሳይንስ ተግባር የራሱ አንፃራዊ መገለጫዎች አሉት፡፡ የዚህ ጽሁፍ ትኩረት ተግባርን በተለያዩ ዘርፎች በሀሳብ ለመተንተን ሳይሆን የራዕይ ጥበብ 2017 ስኬት የሚወስነው በተግባር በምንፈጽመው ድርጊት በመሆኑ ከራሳችን ጋር በማስተሳሰር እንድንወያይበት መነሻ ሀሳብ ለመስጠት ነው፡፡

በራዕይ ጥበብ 2017 ተግባር እንዲመዘገብ የተፈለገው ውጤት በቅድሚያ ተለይቶ ይህን የተለየ ውጤት ለማምጣት የሚሰራን ስራን የሚያካትት ነው፡፡ በመሆኑም እንዲሁ በዘፈቀደና ደራሽ ሆኖ የሚመጣን ጉዳይ መፈፀምን አያቅፍም፡፡ ስራውን የሚሰራው ሰው ሊያመጣ የተፈለገውን ውጤት ግልጽ ባልሆነበትና ስራውና ውጤቱ እንዴት እንደሚተሣሠሩ ግልጽ ባልሆነበት አግባብ ተግባር ብሎ ነገር የለም ይላል የራዕይ ጥበብ 2017 መስመር፡፡ ውጤቱና ውጤቱ እንዲመጣ ያደረገው ዋነኛ ስራ ወይም ድርጊት በተሳሰረና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተሳስረው ሲቀርቡ ድርጊቱን ተግባር እንደተፈፀመ ይወሰዳል፡፡ ይህ እሳቤና መስተሳሰር በሌለበት የሚሰራ ስራ ትርጉም የለሽና ፈፃሚውን የሚያደክም እንጂ ምንም ዕድገትና መነሳሳት የማይፈጥር ነው፡፡ ተግባር የውጤት መንስኤ ሲሆንና ውጤቱም ከተግባሩ በፊት የተለየ መሆኑ ወሳኝ ጉዳይ ነው፤ እንዲሁ ውጤት ስለመጣ ተግባር አለ ማለት ስለማንችል፡፡

በዚህ የራዕይ ጥበብ 2017 የተግባር እይታ መሠረት መምህራን በሚያስተምሩት ዘርፍ ተማሪው እንዲማረው የተፈለገውን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት በሚገባ ለይተው ይህ ውጤት እንዲመዘገብ ክፍል ውስጥ በፈተናና በቤተ-ሙከራ መስራት ያለባቸውን ስራ በማወቅ ሲሰሩ የማስተማር ተግባር ፈፀሙ እንላለን፡፡ ነገር ግን ተማሪው ጋር እንዲመጣ የተፈለገውን ለውጥና ያን ለውጥ ለማምጣት የነሱ ተግባር ምን መሆን እንዳለበት ሳይለዩና ሳያውቁ የሚሰሩት የማስተማር ስራ የማስተማር ተግባር ሳይሆን ከንቱ ልፋት ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ምርምርም ሆነ የማህበረሰብ አገልግሎት ተግባር ፈፀሙ የምንለው በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ሊያስመዘግቡት የፈለጉትን ውጤቶች ለይተው እነዚህ ውጤቶችን የሚያመጡ ስራዎችን ሲሰሩ ብቻ ነው፡፡

በተለያዩ እርከን የሚገኙ አመራሮችም ሊያስመዘግቧቸው የፈለጓቸውን ውጤቶች ከለዩ በኋላ እነዚህን ውጤቶች ለማምጣት መስራት ያለባቸውን ስራ ለይተው ከሰሩ የአመራር ተግባር ፈጽመዋል ብሎ ይወሰዳል፡፡ ራዕይ ጥበብ 2017 ቀድሞ የተለየን ውጤት ለማምጣት የማይሰራ አመራር ሁሉ ደጄ ሁሉ መንገዴ የሆነ ባዛኝ ነው፡፡ በቀላሉም የመለዋወጥ ባህሪና መዋዥቅ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ዕቅዴን እንዴት ላቅደው? እንዴት ዕቅዴን ላጋራው? በምን አይነት መንገድ የስራ ስምሪት ላድርግ? ክትትልና ድጋፌን በምን መንገድ ልስራው? በማለት የሚፈለጉትን ውጤቶች ከለዩ በኋላ ውጤቶቹ እንዲመጡ መሰራት ያለባቸው ስራዎች ሲሰሩ የአመራር ተግባር ተፈጽሟል ማለት ይቻላል፡፡

ተግባርን ከላይ በገለጽነውና በተወሰኑ ምሳሌዎች መሠረት የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ ሊወያይበት፣ ሊያዳብረውና ሊያሻሽለው ይገባል፡፡

ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!

**እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!**

# አበይት ዜናዎች...

## ለመጀመሪያ ዓመት ሴት ተማሪዎች የህይወት ክህሎት ስልጠና ተሰጠ

በአምሳሉ ጥላሁን

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስርዓተ ጾታ ጽ/ቤት ይህን ችግር ለማቃለልና አዲስ ሴት ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑና የግቢ ውስጥ ማህበራዊ ግንኙነታቸው ጠንካራ እንዲሆን የሚያግዝ የሁለት ቀን የህይወት ክህሎት ስልጠና በሁሉም ግቢዎች ሰጥቷል፡፡

ማንኛውም ሰው አካባቢውን ለቆ ወደ ሌላ ቦታ በሚሄድበት ወቅት የአካባቢው የአየር ሁኔታ፣ ባህል፣ ኃይማኖት እንዲሁም ብቸኝነት ለአዕምሮ ሰላም አይሰጥም፡፡ በእነዚህና በተለያዩ ችግሮች መሐል ያለ ሰው አስቦ ለመጣበት ዓላማ ጊዜውን በአግባቡ አይጠቀምም፡፡ ምክንያቱም በዩኒቨርሲው፣ በከተማው ውስጥ ያሉትን ሁነቶች በአግባቡ እስኪያውቅ ድረስ የተለያዩ ችግሮች ይገጥሙ-ታል፡፡ በተለይ ደግሞ እነዚህን መሳይ ችግሮች ለአዲስ ገቢ ሴት ተማሪዎች የሚያደርሱት ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡

የሥርዓተ-ፆታ ጽ/ቤት ዳይሬክተር ዶ/ር አልማዝ ጊዜው ከተለያየ ቦታ ቤተሰቦቻቸውንና አካባቢያቸውን ለቀው የመጡ ተማሪዎች በግቢ ውስጥና ውጭ ለሚገጥሟቸው የተለያዩ ችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ዘዴዎችን እንዲረዱ፣ ለችግሮች ተጋላጭ የሚያደርጓቸውን ምክንያቶች አስቀድመው ማስወገድ እንዲችሉና በዩኒቨርስቲው ቆይታቸው ወቅት በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ እንዲሁም በግቢ ውስጥ ማህበራዊ ግንኙነታቸው ጠንካራ እንዲሆኑ ታስቦ ስልጠናው እንደተዘጋጀ ገልፀዋል፡፡

ሴት ተማሪዎች ከሰዎች ጋር ያለው መስተጋብር፣ የአቻ ግፊትን እንዴት መቋቋምና

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

## በተማሪዎች የተሰሩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ሥራዎች ተጎበኙ

በታድዬ አስማረ

የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግና ሂሳብ ትምህርት ማሰልጠኛ ማዕከል (STEM) በቤተ ሙከራ ውስጥ የተሰሩ የተማሪዎች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ለዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች አስጎበኙ፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ በጉብኝቱ ላይ እንደተናገሩት በቤተ ሙከራው የተግባር ሥራ እየሰሩ የሚገኙ ተማሪዎች ወደፊት የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ እና የምርምሩን ዘርፍ የሚመሩ ታላላቅ ሰዎች እንደሚሆኑ ያላቸውን ተስፋ ገልፀዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው በበኩላቸው ማዕከሉ ተማሪዎቹ ለሳይንስ ትምህርት ከፍተኛ ፍቅር እንዲያድርባቸው እና የፈጠራ ሰዎች እንዲሆኑ ከዩኒቨርሲቲው መምህራንን ከ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን ጋር በመጣመር የሳይንስ ትምህርትን ቀላልና አዝናኝ በሆነ መልኩ ለ45 ቀን በክረምቱ ወቅት እየሰጠ ይገኛል ብለዋል፡፡ ተማሪዎቹ አመቱን ሙሉ ወደ ማዕከሉ በመምጣት ከመምህራኖቻቸው ጋር እንዲገናኙ በማድረግ በማዕከሉ እየሰራ እንደሚገኝ ዶ/ር ተስፋዬ ተናግረዋል፡፡

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

## የዘር ብዜት ስርጭት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንደሚያስችል ተገለጸ

በታድዬ አስማረ እና በአምሳሉ ጥላሁን

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የዘር ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (ISSD) በአማራ ክልል በአራት ዓመታት በዘር ብዜትና ግብይት ላይ ያከናወናቸውን ተግባራትን አስመልክቶ የዘርፉ ባለሙያዎችንና የሚመለከታቸውን ኃላፊዎች በመጋበዝ ውይይት አካሄደ፡፡

በውይይት ላይ የተቀናጀ የዘር ብዜትና ግብይት ፕሮግራም በክልሉ የሰብል ዘር ዘርፉና ከማጠናከር አንፃር በአራት አመቱ የሥራ እንቅስቃሴ የተገኙ ውጤቶችን፣ መልካም ተሞክሮዎች እና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ተዳሰዋል፡፡ መልካም ተሞክሮዎችን በማጠናከር እና የታዩ ተግዳሮቶችን ነቅሶ በማውጣት የመፍትሄ አቅጣጫ የተሰጠ ሲሆን ወደፊትም ከሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ አተገባበር ጋር አቀናጅቶ የግብርናውን እድገት ለማፋጠን ያማከለ መሆን እንዳለበት ተገልጿል፡፡

የተቀናጀ የዘር ብዜትና ግብይት ፕሮግራም በክልሉ ውስጥ ሥራውን ሲጀመር የዘር ብዜትና ግብይት ማጠናከር ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን እ.ኤ.አ በአሁኑ ጊዜ 73 የዘር ብዜትና ግብይት ማህበራትን በስምንት ወረዳዎችና ዞኖች ለማቋቋም ችሏል፡፡ ይህ እድገት ሊታይ የቻለው ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በክልሉ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች በሚያካሄዱት የምርምር ሥራ ጭምር ሲሆን የምርምር ተቋማትና የወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች እገዛም ከፍተኛ እንደነበረ በውይይት መድረኩ ተጠቁሟል፡፡

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

## ዓለም አቀፍ የሥነ ህዋ ሳይንስ ሲምፖዚየም በአፍሪካ ለሁለተኛ ጊዜ ተካሄደ

በየማነ ገብሩ

14ኛው ዓለም አቀፍ የስፔስ ሳይንስ ሲምፖዚየም ከ40 ዓመታት በኋላ በአፍሪካ ለ2ኛ ጊዜ ተካሄደ፡፡ በሲምፖዚየሙ ላይ ከሃያ አምስት ሀገራት የመጡ የስነ-ህዋ ተመራማሪዎች፣ ሳይንስቲስቶች እና ተማሪዎች ተሳትፈዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትና የስፔስ ሳይንስ ተመራማሪ ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ በሲምፖዚየሙ መክፈቻ ላይ እንደተናገሩት ኢትዮጵያ የቀደምት ስልጣኔ ባለቤትና ለአፍሪካ ህብረት መመስረት ግንባር ቀደም ሚና በመጫወት ለአፍሪካውያን ብሎም ለአለም ምሳሌ የሚሆን ረጅም ታሪክ ያላት ሀገር መሆኗን ጠቁመው የነበራትን ሥልጣኔና ሀያልነት እንዲሁም ዓለም በአሁን ሰዓት እየተጠቀመበት ያለውን በስነ ህዋ የምርምር ሳይንስ እና የቴክኖሎጂ ውጤት ተጠቃሚ በመሆን ከሰለጠኑ ዓለም ተርታ እንዳትሰለፍ የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ይህንን ዓለም ዓቀፍ ይዘት ያለው የስነ-ህዋ ሳይንስ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳድረን በኢትዮጵያ እንዲካሄድ መደረጉ ሶስት መሰረታዊ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ዶ/ር ባይሌ ተናግረዋል፡፡ አገሪቱ አሁን ያለችበት ሁለንተናዊ ለውጥ እንደማሳያ መጠቀም፣ በዘርፉ ዩኒቨርሲቲው እያስተማራቸው ያሉ ተማሪዎች ከነዚህ ሳይንስቲስቶች ልምድ እንዲያገኙ በማድረግ ሳይንሱን በደንብ እንዲያውቁ ማድረግ እና በስነ-ህዋ ሳይንስ የሚመራመሩ ኢትዮጵያዊያን ያለምንም ውጣ ውረድ በሀገራቸው በተዘጋጀው ዓለም አቀፍ ሲምፖዚየም ተገኝተው አሁን ዓለም እየተጠቀመበት ያለውን የቴክኖሎጂ ውጤት በአገራችን በቀላሉ በማላማድና ቴክኖሎጂውን ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል እውቀት ማስገኘት ነው ብለዋል፡፡

በአሜሪካ ቦስተን ኮሌጅ የሥነ ህዋ ተመራማሪና የሲምፖዚየሙ ዓለም አቀፍ አስተባባሪ ዶ/ር እንዳወቀ ይዘንጋው የስነ-ህዋ የምርምር ውጤት የሰው ልጅ የእለት ከእለት ተግባራቱ ላይ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸው ይህንን የስነህዋ ሳይንስ የምርምር ሥራ በኢትዮጵያ መሰረት ኖሮት ዓለም አሁን የደረሰችበት ደረጃ ላይ አገሪቱን ለመቀላቀል ከመቀሌ፣ ከባሕር ዳር እና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሙሁራን ከቦስተን ዩኒቨርሲቲ ጋር አብረው እየሰሩ መሆናቸው ተናግረዋል፡፡

ሲምፖዚየሙ በኢትዮጵያ መካሄዱ ለዋሽራ ስፔንስ ሳይንስ ላብራቶሪ ማዕከል ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው የገለጹት በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የማዕከሉ ተመራማሪ ዶ/ር መልሰው ንጉሴ በማዕከሉ ያሉት ተመራማሪዎች እስካሁን የሰሯቸው የምርምር ሥራዎችን ይዘው በመቅረብ ከዓለም አቀፍ ተመራማሪዎች ገንቢ የሆነ ግብረ መልስና እውቀት ገብይተዋል ብለዋል፡፡

‘Magnetosphere-Ionosphere Thermosphere coupling impact at low and mid-latitudes’, ‘Longitudinal dependence of equatorial electrodynamics and storm-enhanced density’, ‘Lonospheric irregularities and scintillations’, ‘New results from recently deployed instrumentation’, ‘Equatorial aeronomy related to atmosphere ionosphere coupling’ and ‘Future opportunities using upcoming new mission and planned ground-based instrumentation’ በሚሉ ስድስት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ ምሁራን ጥናታዊ ፅሁፍ በማቅረብ በተሳታፊዎች ሰፊ ውይይት ተደርጐባቸዋል፡፡

## ዓለም አቀፍ ጉባኤ ተካሄደ

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ኮሌጅ በሂሳብና እና በስታቲስቲክስ ትምህርት ላይ ያተኮረ አለም አቀፍ ጉባኤ “Improving Quality and Introducing Technology at all Academic Levels in Africa” በሚል መሪ ቃል ለአራት ተከታታይ ቀናት አካሄደ፡፡

በጉባኤው መክፈቻ ወቅት የኮሌጁ ዲን አቶ አንዳርጌ ጌራወርቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተካሄደው ጉባዔ የሚገኙ እውቀት፣ ክህሎትና ተሞክሮዎችን በመጠቀም የዩኒቨርሲቲውን እቅድ እናሳካለን ብለዋል፡፡

በመርኃ ግብሩ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ምክትል ዳይሬክተር ጀኔራል ወ/ሪት አበራሽ ታሪኩ ኤጀንሲው በስታስቲክስ እድገት ላይ ብሄራዊ ስልታዊ እቅድ ቀርፆ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑን ገልፀዉ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አስፈላጊና ወቅታዊ በሆነ ጉዳይ ላይ ጉባዔ ማዘጋጀቱን በማድነቅ ምስጋናቸውን ለዩኒቨርሲቲው አድርሰዋል፡፡

በጉባኤው በተለያዩ ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የሚገኙ ተቋማት ምሁራን ተገኝተው በስታቲስቲክስና ሂሳብ ትምህርቶች እንዲሁም ተያያዥነት ባላቸው ርዕሶች ዙሪያ ሰፊ ጥናታዊ ጽሁፎች ያቀረቡ ሲሆን በተሳታፊዎች ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

## My Reflection

# Are we really busy?

Yenus Nurie (Department of English Language and Literature)

The past has gone by leaving its scar on each part of our lives. Whether we like it or not, we are the victims of our passion towards killing our own time. In fact, no special skill is required to realize ourselves if we pause for a moment and think where we are heading. Today we have the time and opportunities to drastically change our lives. Remember! This day is destined only for those who do not discard their own true being, but it is for those who double check their commitment for a change to come. Today is not for those who exchange their time with no sign of struggle to explore their entire vision to come to true. Definitely the day belongs to those who revisit their daily deeds and approach their future aspirations.

Given the above realities, the most striking fact comes from the perception we have for ourselves. To begin with, instead of being inspired by our own untold wisdoms and values, we are prone to make up our minds in some inflexible stereotype that could have a potential of disturbing our mentality. Our minds are usually filled with: "time management is theirs" narrative as if we lack the capacity to manage time. Sometimes, my attention is drawn to ask myself how we underestimate ourselves far from our values. On the other hand, I assume that the problem rests with us when I usually realize that our words are more ironic than we can possibly do. In simpler terms, I am concerned with how we are echoing what others say as we don't have our own value. In short, unable to see ourselves and unwilling to go out of our comfort zones, it has been hard for us to imagine what our life would have been like if we had been figuring out who we are and what we could potentially do.

Distorted by these contradictions, we apprehensively fail to preserve our national value. In this case, the crucial test of many of us is; therefore, the need that we have to acknowledge our own fault and redress our fixed views. This presses us to ponder a more basic question: How can we bear the sheer illogicality of our deductions: "I am busy" when we have possessed an abundance of time. In the first place, it seems to me that we miss the significance of time management. Subsequently, let us not forget that to miss the significance of time management today is to further complicate our future prospects.

*Turning the past evils into advantages has apparent vitality to undertake the course of remedial action for a better future.*

In some respects, I heard some people complaining about the misuse of their time. Nevertheless, self condemnation against the spontaneous practices should be afforded by an immediate response to change ourselves before being overwhelmed by an uncertain future. Neither complaining against the past nor withdrawing from the race and lapse into silence cultivates anything. Instead, turning the past evils into advantages has apparent vitality to undertake the course of remedial action for a better future. To put the point quite simply, we need to exhibit the real potency of our own moral outlook to bear a more justifying success.

We may say that we are busy all the time. But, to be honest, what we claim that we are busy sharply contradicts with what we really do. For the reasons that seem inherent to our daily realities many of us claim a shortage of time, yet we all have it in abundance. For example, we simply muse upon our emotions and wistfully allow our thoughts to meander here and there. We are always wasting our time on non-work activities such as staring at face book and twitter pages for so long, excessively watching videos and playing software games. As a result of which we let our work pile up, which in turn alerts us to the risk of being the 'real busy'.

Undoubtedly, such kind of trend will negatively affect for the institution that has been devoted to achieving its ultimate vision by 2025 to be one of the top ten research universities in Africa. The outcome will be devastating, especially when its staff is no better at time management than any other people. Frankly speaking, I sometimes feel that we are worse in time management than other public schools. Some of us arrive too late for work, yet we feel we are so busy all the time. While there is a widespread perception that life is busier than ever for every one of us, we hear some complaints from our customers here and there as their work never ends. The other surprising point that is usually echoed from some officers to customers is: "We are busy" when they are doing nothing. In essence, this kind of self denial and deceptive action has the potential to jeopardize the relationship between the institution and the customers.

The staff and all the community in the university need to be on the side of the customers' feeling at least for the sake of our common national goal. For the detailed account of reflections, I shall come in another paper, our expectations of customers to lower their gaze and bow to us when they need service has dangerous implications for the success of our missions. Although I understand that greetings and smiles have the power of touching the feelings of people, sweeping aside our virtue to serve them is capable of wrecking the image of the institution. All in all, emotion and contempt need to be replaced by logic and commitment that can amplify the better images of the institution so that we can achieve our goals. Otherwise, the dreadful calculations we unintentionally make at the expense of promoting real services will not lead us beyond wishful thinking.

In general, we can attain an inspirational success only when we manage our time and use it as leverage for flourishing dedicated enthusiasm to a better future. Indeed, there is no secret to failure, but failure to understand our current reality and strengthen it begets another failure that has a cascading effect on dwindling with our potentials which may be unable to be restored throughout years to come.

# የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

(ከመስከረም ወር ዕትም የቀጠለ)

በፈታሒ በቃሉ
Fetahi1717@gmail.com

ተስፋሁን ከእስር ቤት ከተፈታ በኋላ በነበረው ድርጊቱ በመፀፀት የእናቱን አደራ ለመወጣት በትምህርቱ በርትቶ ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ ቆርጦ ቢነሳም አልፎ አልፎ በጥናቱ ላይ የሔርሜላ ሁኔታ ድቅን እያለበት እያቅበጠበጠው ከመሆኑም ጋር ተያይዞ ከጊዜው ጥበት አኳያ የቱን ትቼ የቱን ላንሳው በሚል በተደጋጋሚ መንታ ሀሳቦች ተጠምዶ እየተሰቃዬ ይገኛል፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ ባላሰበው መንገድ ጓደኛዋን አግኝቶ ባስተላለፈው የቀጠሮ መልዕክት ለተወሰኑ ጊዚያቶች በአካል ስላገኛት ሲያወሩ ቆይተው መለያየታቸውን ባለፈው ጊዜ መከታተላችን አይዘነጋም፡፡ ቀጣዩን ደግሞ አብረን እንከታተል………………

ከሔርሜላ ጋር አብረን ቆይተን ሸኝቻት ከተለየቸኝ በኋላ ለራሴ አሁን ምን ቸገራት አብራኝ ብትቆይ፡፡ እንዲያው ሁልጊዜ እንደ ጥዋት ጤዛ ታይታ የምትጠፋበት ምክንያት ምንድን ነው? ደግሞስ አሁን የዛሬው ክላስስ ቢቀርባት ምናለበት? በማለት ራሴን እየጠየቅሁ ለብቻዬ እያወራሁ ስሄድ ከፊት ለፊቴ የሆኑ ተማሪዎች ሲሣሣቁ ቀና ብዬ ስመለከት ሣላስበው ወደ ምኝታ ቤቴ የሚወስደውን በመተው የምግብ ቤቱን መንገድ ተከትዬ እየሄድኩ እንደሆነ ሣውቅ፣ በድፍረት እንደመቆም አልኩና ተመልሼ ወደ ምኝታ ቤቴ አመራሁ፡፡

ከሰዓት በኋላ ትምህርት ስላልነበረን የነበረውን ሁኔታ ለሣጅን ለመንገር ወደ ምኝታ ቤት ስገባ ከአንድ ጓደኛችን በስተቀር ማንም የለም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ወደ ቤተ መጽሐፍት ገብተዋል፡፡ እኔም በደመ-ነፍስ በቀጥታ ወደ ቤተ መጽሐፍት ሄድኩና የአናቶሚ መጽሐፍ አነሣሁና በመቀመጥ ትንሽ እንዳነበብኩ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በመካከላችን የነበረው ትዕይንት እየመጣ ድቅን እያለ አስቸገረኝ፡፡ ደግሞ እኮ ለብርቱ ጉዳይ ስለምፈልግህ ያለችበት ምክንያት ምን ሊሆን? ነው፡፡ ይሄኔስ እሷንም እንደ እኔ ግራው ገብቷት ይሆናል? ማን ያውቃል? በማለት አሰብኩና ልቤ በደስታ መፈንደቅ ያዘች፡፡ ትንሽ ቆየሁና በተቃራኒው በማሰብ ምን አልባት ሌላ ልትጠይቀኝ የፈለገቸው ነገር ይኖር ይሆን? ምን ዓይነት ሰው ናት? ደግሞ ዛሬ በስንት ፍለጋ ብትገኝ ሌላ የቤት ሥራ ሰጥታኝ ትሄዳለች ወይ ጉድ በማለት ሳወጣ ሳወርድ አንድ ገጽ እንኳን ሳላነብ ሰዓቱ ነጎደ፡፡ ወዲያው አንብቤ መገንዘብ እንዳልቻልኩ ሲገባኝ የያዝኩትን መጽሐፍ ወደ መደርደሪያው በመመለስ ስወጣ ቀኑ እየመሸ ሄዶ የእራት ሰዓት ስለደረሰ እነ ሣጅንም ወደ ምኝታ ቤት መጡ፡፡ ከዚያም ሣጅን ጠራኝና እንዴት ነው? እየተረጋጋህ ነው? ወይንስ አሁንም ችግር አለ? በማለት ጠየቀኝ፡፡ እኔም ችግር እንደሌለ ስገልፅለት ፈገግ እያለ ወደ እራት አንሄድም? እንዴ አለኝ፡፡ እሽ አልኩትና ተያይዘን እያወራን ስነሄድ ‹‹ለሻሼ ደወልህላት›› አለና ሞባይሉን እያወጣ ሲጠይቀኝ ራሴን በመነቅነቅ አለመደወሌን ሳሳውቀው ደወለና አገናኜኝ፡፡ ከዚያም ሰላምታ ተለዋወጥንና ነገ ጠዋት 1:30 ላይ በር ላይ እንድጠብቃት በመንገር ቻው ብላ ተሰናበተችኝ፡፡

ሣጅን እና እኔ እራት በላንና ስንወጣ ሔርሜላን እንዳገኜኋት ስነግረው ደንገጥ ብሎ በመገረም ዓይነት የት? አለኝ፡፡ እኔም ሁኔታውን በዝርዝር ነገርኩት፡፡ እሱም ቀና ብሎ እየተመለከተኝ “ታዲያ ለምንድን ነው ጠፍታ የከረመችው?……›› ብሎ ሲጠይቀኝ ያው በመገናኛ ችግር ነዋ! በማለት ስመልስለት ሣቀና በአንድ ዩኒቨርሲቲ ለዚያውም በአንድ ግቢ እየተኖረ መጠፋፋት! ካለ በኋላ ለመሆኑ በእሷ ምክንያት ለዚህ ሁሉ ችግር መዳረግህን አስረዳሀት? አለኝ እኔም እየሣቅሁ እሱን ለመንገር ጊዜው ገና ነው፡፡ እንዲያውም ለብርቱ ጉዳይ እንደምትፈልገኝ ነግራኝ በችኮላ ወደ ክላስ መግባቷን አወራሁት፡፡ ሲያዳምጠኝ ቆየና “ታዲያ በለስ ቀንቶኛል አትለኝም?” በማለት ቀለደብኝ፡፡ በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ምክር ነገር ስጠይቀው በሩቁ እየተመለከተ ትንሽ ቆዬና ለመሆኑ አንተ ምን አሰብህ? በማለት ጥያቄዬን በጥያቄ መለሰልኝ፡፡ እኔም ፈጠን ብዬ እንደ ምንም ተደፋፍሬ እንደምወዳት እነግራታለሁ፡፡ በማለት ስመልስለት “ልክ አይደለህም፡፡ መጀመሪያ ተረጋጋ ከመጀመሪያው እወድሻለሁ እወድሃለሁ የሚለው ቋንቋ ጊዜውን ጠብቆ ሊመጣ የሚችል ጉዳይ ነው፡፡” አለና በመቀጠል “ምን አልባት በሂደትም ቀስ በቀስ ልትተዋወት ስለምትችል አትቸኩል፡፡” በማለት ህሌናዬ ሊቀበለው የማይችል ሀሳብ ተናገረ፡፡ በአዕምሮዬ እንድተዋወት የሚያስችለኝ አንድም ነገር ያለ አይመስለኝም፡፡ ብቻ ለሁሉም በሚቀጥለው እፈልግሃለሁ ስላለች ለምን እንደፈለገችኝ ከእሷ ከራሷ አንደበት ስሰማ የሆነ ፍንጭ አገኛለሁ በማለት በሀሳብ ተውጬ እያብሰለሰልኩ እያለ እንዴት ነው? አይመስልህም አለና አባነነኝ፡፡ እኔም በደመ ነፍስ እሽ ይሁን አልኩት፡፡

ሣጅን ትንሽ ዝም ብሎ ቆዬና ትምህርቴን ሳልዘናጋ መቀጠል እንዳለብኝ እያለሳለሰ ብዙ እየመከረኝ ሳናስበው ብዙ ተጓዝን፡፡ ከዚያም ርዕሳችን ለመየቀር በማሰብ፣ እናቴ ደብዳቤ እንደፃፈችልኝና ከአገር ቤት በመውጣት ያቋረጠችውን ትምህርት ለመቀጠል መፈለጓን ሳወራው ወደ እኔ አተኩሮ እየተመለከተ እንዴት ነው? እናትህ ባለ-ሙሉ ወኔ ናቸው ማለት ነው፡፡ አለና አከታትሎ ታዲያ ደስ አይልም? በማለት እጁን በመዘርጋጥ ጠበቅ አድርጎ በመጨበጥ ስለማያውቃት እናቴ አድናቆቱን ገለፀልኝ፡፡ በእውነቱ እኔም ሁኔታውን እንደገና ሳጤነው የበለጠ ደስ አለኝ፡፡

በነጋታው ጠዋት ሻሼን ከዋናው በር ላይ ቆሜ ስጠብቃት ቀጠሮ አክብራ በመምጣት ቀደም ሲል በገባችልኝ ቃል መሠረት የሞባይል አፓራተስ ከሲም ካርድ ጋር አበረከተችልኝ፡፡ ከሰጠችኝ በኋላ «ዓይን ዓይኔን እየተመለከተች» ከእሥር ቤት ከወጣህ ወዲህ ትምህርት እንዴት ይዞሃል? በማለት ጠየቀችኝ፡፡ እኔም ደህና እየተከታተልኩ እንደሆነና ስለተደረገልኝ ስጦታ ምስጋናዬን አቅርቤላት ለተወሰኑ ጊዚያት ስናወራ ቆይተን ለሥራ ስለምቸኩል ሲመችህ ደውልልኝ በማለት ተሰናብታኝ ሄደች፡፡

እንደሄደች ምን ያህል ደግና የዋህ እንደሆነች እየገረመኝ የተሰጠኝን ሞባይል እያገላበጥኩ በመመልከት ስጓዝ አንድ ፕሮክተር በችኮላ መጣና ትፈለጋለህ? አለኝ ማን እንደፈለገኝ ስጠይቀው ፖሊስ በማለት አስደነገጠኝ፡፡

ወዲያውኑ ቆም በማለት እነዚህ ሰዎች አሁንም አልተውኝም ማለት ነው? አልኩና ፖሊሱን ከማግኘቴ በፊት ሣጅን ማወቅ ስላለበት ስልኬን አወጣሁና ለሣጅን በመደወል እንዲመጣ አደረግኩ፡፡ እንደመጣ በፖሊስ መፈለጌን ስነግረው ተረጋጋ? ምን አልባት ከአንተ የሚፈልጉት መረጃ ስለሚኖር እንጅ በሌላ ጉዳይ አይፈልጉህም በማለት ድፍረትና ሞራል ሰጠኝ፡፡ ወዲያውኑ አብረን ተያይዘን ስንሄድ ፖሊሱን ከፕሮክተሮች ጽ/ቤት ተቀምጦ አገኘነው፡፡ ፖሊሱም ሰላምታ ከሰጠን በኋላ ትንሽ ብጣሽ ወረቀት አወጣና ከሦስት ቀን በኋላ ለምስክርነት ባሕር ዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት እንድገኝ የተጻፈ መጥሪያ መሆኑን በመንገር በቀሪው ላይ አስፈርሞ ሰጠኝ፡፡ ምንም እንኳን ሣጅን ቢያረጋጋኝም መጀመሪያ በፖሊስ መፈለጌን እንደሰማሁ በጣም ፈርቼ ነበር፡፡ ነገር ግን የተፈለግኩበትን ምክንያት በደንብ ስረዳ በመጠኑ ተረጋጋሁ፡፡

ይቀጥላል!

# የግጥም ጥግ

## ዓለም በምርጫዋ…

አለም በታሪኳ በአንድ ዘመን ምዕራፍ፣

የምርጫዋ ስህተት በእውነት ቃሉ ሲፃፍ

በርባን ወንበዴ ነው ሀገር ያሰለቼ፣

ሰላም የሚነሳ ለሰው ያልተመቼ፡፡

ሁከትና ሽብር አመፅ አስነስቷል፣

በጭካኔ ዱላው ብዙ ነፍስ አጥፍቷል፡፡

በዚህ አድራጎቱ ወህኒ ገብቶ ታስሯል፣

እየሱስ ፃዲቅ ነው ፍቅር የተጠማ፣

በመልካም አንደበት ሲሰብክ የተሰማ፡፡

ድውይ የፈወሰ እውራን ያበራ፣

ክፋትን ኮንኖ መልካምን የሰራ፡፡

ለሰው ልጅ መድህን በምስራች ቃሉ፣

ብዙ ምንዱባኖች እረፍት የተሞሉ፣

ሲከተሉት ነበር «ሆሳዕና ሆሳዕና» እያሉ፡፡

ጲላጦስ በወንበር ለፍርድ ተቀምጦ፣

የከሳሽ… ተከሳሽ ግራ ቀኝ ተዳምጦ፡፡

«ማንን ልፍታላችሁ እንደ ህጉ ልማድ፣

ጥፋት አላየሁም በዚህ ሰው ለመፍረድ»

ብሎ ቢናገርም ፍርድ እንዳይዛባ፣

የኢየሱስ ከሳሾች ያሴሩበት ደባ፡፡

«በርባንን ፍታልን ይህንን ስቀለው

…ከምድር አስወግደው»

ብለው ሲማፀኑት…

የህዝብ ድምፅ ይከበር ነውና ነገሩ፣

በርባን ከወህኒ ቤት… ወጥቶ ከነ ግብሩ፡፡

አለም በምርጫዋ የልመናዋን ቃል
ወስዳዋለችና፣

ዛሬም ሁከት አለ ዛሬም ሽብር አለ
በምንሰማው ዜና፣

ጦርነት ሽብር ነው የሰው ልጅ ፈተና፡፡

ደስታ ተከስተ (BDU. Security service)

# ገጠመኝ

አለባቸው አስፋው (ከቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ)

ማለዳ ተነስቼ እንደወትሮዬ በመስኮት አንገቴን ሰገግ አድርጌ ውጭውን ተመለከትኩ። ቀኑ ውብ ነው። ለአዲስ ጉዞ ይህ ስሜት የምፈልገው በመሆኑ ደስታ ቢጤ በውስጤ ሲሰራጭ ተሰማኝ። ቁርሴን ቀማምሼ የተለመደችውን ቦርሳዬን አንጠልጥዬ አዲስ ወደተመደብኩበት መስሪያ ቤት የመጀመሪያ ቀን ጉዞዬን ጀመርኩ። መስሪያ ቤቱ ግርማ ሞገሱ የሚያስፈራ እዚያ መሥራትም የሚያኮራ ስለነበር በውስጤ የሚመላለስ ብዙ ነገር ነበር። ዕድሜዬ የባጀባቸው ያለፉት መስሪያቤቶች ሲያተክሩኝ ስለነበር ከዚህ በኋላ ቅጥ ያለው ተግባር እየፈጸምኩ ምን ያህል እንደማርፍ ተሰምቶኝ ውስጤ በደስታ እየተፍነከነከ አዲሱ መ/ቤት በር ላይ ሳላስበው ደረስኩ። በሩን ሳየው ቀድሞ እንዳላየሁት ሁሉ እያደነቅሁ ወደ ውስጥ ዘልቄ ገባሁ። እንዳአጋጣሚ ሆኖ እኔ ስደርስ ግን በግቢው ውስጥ አንድ ትልቅና ታዋቂ ሰው አርፎ ኖሮ አለቃ ከምንዝር ሲተረማመስ ነበር። ከቤቴ ይዤው የወጣሁትን የደስታ ድባብ ቢያናጥብብኝም ሰው ሲሞት ያሳዝናልና የሞተው ማንና በምን ምክንያት መሆኑን ለማጣራት ጠጋ ብዬ ሰዎችን መጠየቅ ጀመርኩኝ። አንድ ኑሮ ያልተመቻቸውና ለሞት የቀረቡ የሚመስሉ አዛውንት አይናቸውን እየጨመቁ ንፍጣቸውን እየጠረጉ ሟቹ አቶ ለውጤ መሆናቸውን ነገሩኝ። ሰው እንዴት ህዝብ በሚተራመስበት ሊቃውንትና ባለስልጣናት ካሉበት አደባባይ ላይ ይሞታል ብዬ እየገረመኝ ነገሩን የበለጠ ለማጣራት የአቶ ለውጤ አስከሬን አለበት ወደተባለው የመስሪያ ቤቱ ሹማምንት መሰብሰቢያ አዳራሽ አቀናሁ።

ወደ አዳራሹ ስገባ ሱፍና ክራባት የለበሱ ቦርጫምና ቦርጭ የሌላቸው ወንዶችና በሱሪ፣ በአጭር ቀሚስ፣ በባለተረከዝ ጫማ ያጌጡ ሴቶች በከበቡት ጠረጴዛ መሃል ፊታቸው ብቻ እየታዬ የአቶ ለውጤ አስከሬን ተጋድሟል። ገርሞ ገረመኝ። ‹‹እኝህማ እኔ በቅርቡ የለቀቅሁት መስሪያ ቤት ውስጥ በሞትና በህይወት መሃል የሚንጠራወዙት ሠው አይደሉም እንዴ? አልኩ ለራሴ።

በዚህ ድንጋጤ ውስጥ ሆኜ ዘወር ስል አንዱ ባለከረባት ዳይሬክተር "መንትያ አላቸው። የኛን መስሪያ ቤት እንዲያግዙ ተልከው የመጡ ናቸው" ብሎኝ እርፍ አለ።

የሥራ ባልደረቦቼን በቅጡ ሳልተዋወቅ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳለን አሟሟታቸውን የሚያጣራ አምስት አባላት ያለው ቡድን ከተፍ አለ።

"ሁላችሁም አንዴ ውጡልን" አለ አዛዣቸው።

ያወቀኝ ባይኖርም አንዱ አዲስ ዳይሬክተር ነኝና ካሉት ሠዎች ጋር ተቀላቅዬ ስወጣ ለማረፊያ የተዘጋጀው ቦታ አስደመመኝ። የወንበሮቹና ጠረጴዛዎቹ ምቾትና ማማር እንዲሁም የአትክልቶቹ ገጽታ ልዩ ነው። ሁሉም በየጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን ቁርስ (ኬክ፣ ቆሎ፣ ኩኪስ፣ ፍራፍሬ ...) እያነሳና ትኩስ ነገር እያዘዘ ቦታ ቦታውን ይዞ እያውካካ ያዝን ጀመር።

ደግሞ ገረመኝ - የታዋቂውና

> አዝናኝ ቀልዶች ባሉበትም
> ቀልባቸው ያየኛል ባልኩበትም
> በሌሉበትም አቅርቤያለሁ። በሳቸው ስም
> ስብሰባ ተጠርቶ ቀርቼባቸው አላውቅም። ...
> አሉ በተባለበት ሁሉ እየተገኘሁ የስብሰባ
> ማሟሟቂያ የአፍ ማላወሻ መሟላቱን
> ሳረጋግጥና ጉልበት እንዳያጡ
> ሥሰራ ቆይቻለሁ።

ጉምቱው (ልምድ ያካበተ) ሰውዬ ለቅሶ እንዲህ መናኛ መሆኑ። ታዋቂ ያልኳቸው ዝም ብዬ ሳይሆን እኝህን ሰው በየመስሪያ ቤቱ የማያነሳቸው፣ ጋብዞ የማያስደሰኩራቸው፣ በየዘርፉ ያለ ሹም የሚያሰግድላቸውና የሚያጨበጭብላቸው በመሆኑ ነው። ሰውየው ትልቅ ቢባሉም የሚጠቅም ዘመድ እንደሌላቸው ሸውታው ታወቀኝ። ትንሽ እንደቆየን መርማሪዎቹ ስለአቶ ለውጤ ሞት የቅድሚያ ተጠርጣሪዎችን ለመለየት የመስሪያ ቤቱን የበላይ ኃላፊዎች ማነጋገር እንደሚፈልጉ በመግለጻቸው ሁላችንም ቆሎአችንን እያሻመድን፣ ሻያችንን እየጨለጥን መጠበቅ ጀመርን። የመርማሪዎቹ ሁኔታ ለሞቱ መንስኤ የሆነውን ወገን ከኛ መሃል እንደሚያገኙ እርግጠኛ የሆኑ ያስመስልባቸዋል። ይባስ ብለው ተጠርጣሪ መሆናችንን ሲናገሩ እኔ ዛሬ ገና ግቢው የገባሁ መሆኑን ልናገር ዳዳኝና መልሼ ተውኩት። በመሃሉ አስከሬኑን የያዘው መኪና ሲወጣ አየሁ።

ወዲያው ተጠርጣሪዎችን በስም ለይተው በየተራ እንዲገቡ አዘዙ። በጥሪው ውስጥ የተካተቱት አቶ ትጋት፣ ወ/ት ተግባቦት፣ አቶ ምራው፣ ወ/ሮ ቡድኔና ወ/ሮ ፈጠኑ ነበሩ። ጥሪው እንዳበቃ ከውስጥ አንድ ሌላ መርማሪ ወጥቶ አቶ ጠየቁና ወ/ሮ አመኑም እንዳይሄዱና እንዲጠብቁ ተነገራቸው። ለጥያቄው በቅድሚያ የተጠራችው ሽቅርቅሯና ሳቂታዋ ወጣት ወ/ት ተግባቦት ነበረች። እንደገባች "እኔ አልገደልኳቸውም። እንዲሞቱ የሚያደርግ ነገርም አልሰራሁም" አለች።

ከመጡት ቀጠን ያለው መርማሪ "አልገደልሻቸው ይሆናል ግን እንዳይሞቱስ ምን ድጋፍ አደረግሽላቸው?" አላት።

"የቻልኩትን ሁሉ አድርጌያለሁ፤ አዝናኝ ቀልዶች ባሉበትም ቀልባቸው ያየኛል ባልኩበትም በሌሉበትም አቅርቤያለሁ። በሳቸው ስም ስብሰባ ተጠርቶ ቀርቼባቸው አላውቅም። ፎቶ አንስቻለሁ፤ አሉ በተባለበት ሁሉ እየተገኘሁ የስብሰባ ማሟሟቂያ የአፍ ማላወሻ መሟላቱን ሳረጋግጥና ጉልበት እንዳያጡ ሥሰራ ቆያቻለሁ። " አለች ግንባሯን አኮስትራ።

"እና ይህ እንዳይሞቱ የሚያግዝ ይመስልሻል" አላት ከሷ ትይዩ የተቀመጠው ሌላ መርማሪ። ወዲያው በይ ለጊዜው እዚያ ክፍል ገብተሽ ቆይ ብለዋት አቶ ትጋት ተጠርተው ገቡና እንዳጎነበሱ ቆሙ።

"በአቶ ለውጤ ሞት ተጠርጥረዋልና ምን ይላሉ" አላቸው ወፈር ያለው መርማሪ። አቶ ትጋት እንደስማቸው ትጉ የተመሰገኑ ከሥራ እንጂ ከሰውና ከወሬ የማይደርሱ አቶ ለውጤ ሲሞቱ ሲያጣጥሩም ደርሰው ማኔጅመንቱ እንዲሰባሰብና በጤናቸው ጉዳይ ላይ እንዲመካከር ያመቻቹ ያም ሆኖ ኃላፊዎቹ በሌሎች የማይረቡ የመስሪያ ቤቱ ወሳኝ ጉዳዮች በመጠመዳቸው ፈጥነው ባለመድረሳቸው አቶ ለውጤ ማረፋቸውን ሳግ እየተናነቃቸው አስረዱ። እንዲያውም ከዚህ ቀደምም ብዙ ጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ እያለፉ በአቶ ለውጤ ዕድሜ ላይ ጥቂት መጨመራቸውን እንደሚያምኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እሳቸውም ጤና እያጡ በመሆኑ ኑሮ ለራሳቸውም ትግል እንደሆነባቸው ተናገሩ። ከደከመውም ከበረታውም ጋር ሆኜ የአቶ ለውጤ ልፋት እንዲሰምር፣ ተቋሙ እንዲቀየር፣ እዚህ ያለውን ጨርሰው ለሌላው እንዲተርፉ ለፍቼ ነበር አሉ። ሆኖም የዚህ ግቢ ሰው በወረት የነአቶ ስንፍናና ምንቸገረኝ ጓደኛና ሚስጥረኛ ሆኖ በሽታው እንደሚገድላቸው እያወቀ እምቢኝ አለ። በዓይኔ በብረቱ አይቻለሁ ብዬ ባልምልም ከገደሏቸው ውስጥ እነዚህ ሁለቱ ዘመዳሞች ባይኖሩ "ከምላሴ ፀጉር ይብቀል" አሉና አልናገርም ያሉትን ድንገት ተናግረውት አረፉ። እናም ማልቀስ ሲጀምሩ መርማሪዎቹ ቀድሞ መረጃ ይኑራቸው በጤናቸው ሁኔታ አቶ ትጋት ከነሱ ጋር እንዲቀመጡ ቦታ ሰጧቸውና ተረኛውን አቶ ምራው አስገቡት።

አቶ ምራው ሲተኛ እንኳ ማውለቁን የሚጠረጠረውን ክራባቱን አንጠልጥሎ ከለመደው የሚመች የስብሰባ ወንበር በተለየ የሱ ፀሐፊ ረዳት በምትቀመጥባት ኩርሲ መሰል ወንበር ላይ እየቀፈፈው ተቀመጠ። የጠሩት ሰዎችም ከለመዳቸው ወዛም ሰዎች የተለዩና ‹ውቃቢ ቢስ› የሚባሉ አይነቶች ሆኑበት። ከነዚህ ሰዎች የሚመነጨውም ጥያቄ ለሱ እንደማይመጥን እያንሰላሰለ ሳለ "ለመሆኑ አቶ ለውጤን ማን ገደላቸው ትላለህ" አለው ያው ቀጭን መርማሪ ካጎነበሰበት ቀና ሳይል። "ምን አውቃለሁ፤ እኔንም ገርሞኛል" አለ ዘና ብሎ። ቀጥሎም "የኔ ተግባር እንደሚታወቀው የዚህን ተቋም መስመር አስጠብቄ መመራት ነው። እርግጥ በታሰበው ልክ መራመድ ባለመቻላችን አቶ ለውጤ ሊደግፉን እንደመጡ እናውቃለን። ከበላይ የመጡ በመሆኑም አክብረን ይዘናቸው ነበር። እኔ በተለይ በሄድኩበት የሳቸውን ዝና ሳላወራ ከጎኔ ሳላስቀምጣቸው መንደርደሪያ እንዲሰጡ ሳላደርግ የቀረሁበት ጊዜ የለም። የበታቾቼም በሌሉበት ጭምር እንደሚያወድሷቸው አውቃለሁ። ጤናቸው የሚጠበቀው ከሠራተኛው ጋር ባላቸው ቁርኝት መሆኑን ስለምረዳም የበታች ሹማምንቶቼ እንዲያገናኟቸው ጥብቅ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# እንግዳችን

## “የምርምር አጀንዳ መሆን ያለበት በኛ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ እምቅ ተሞክሮዎችን መዝዞ አውጥቶና ሳይንሳዊ በሆነ መልክ አደራጅቶ በጥቅም ላይ ማዋል ነው። ”

ዶ/ር ዓለማየሁ ቢሻው

**የዚህ ወር እንግዳችን የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ጥናት ጽ/ቤት ዲን ናቸው። የህይወትና የስራ ተሞክሯችውን አስመልክቶ ከናይል ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገዋል። ቃለ መጠይቁን እነሆ። መልካም ንባብ!**

ናይል፡- ዶ/ር ዓለማየሁ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን!

ዶ/ር ዓለማየሁ፡- እኔም አመሰግናለሁ።

ናይል፡- ስለ አስተዳደገዎ፣ ስለ ትምህርት ቤት እና ስለ ትዳር ህይዎተዎ ያጫውቱን?

ዶ/ር ዓለማየሁ፡- የተወለድሁት ዳንግላ ከተማ ነው። በሥራ ምክንያት ወላጆቼ ወደ ግምጃ ቤት ከተማ ሲቀይሩ እኔም እድገቴንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቴን እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ በዚሁ ከተማ አጠናቅቄአለሁ።

በወቅቱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባለመኖሩ ወደ ዳንግላ ተመልሼ ከ9-12ኛ ክፍል ትምህርቴን ተምሬአለሁ፤ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ጥሩ ውጤት በማምጣቴ በቀድሞው ባህር ዳር መምህራን ኮሌጅ በአሁኑ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ገብቼ የከፍተኛ ትምህርቴን አጠናቅቂአለሁ። ከዚያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪዬን በሥርዓተ ትምህርትና ማስተማር ሳይንስ አግኝቻለሁ። የPhD ትምህርቴን በደልሂ ዩኒቨርሲቲ (ህንድ) ተቀብያለሁ። ትዳር መስርቼ የሶስት ልጆች አባት ሆኛለሁ።

ናይል፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ ከመቀጠረዎ በፊት የት የት ቦታዎች ላይ ሰርተዋል?

ዶ/ር ዓለማየሁ፡- ከዩኒቨርሲቲ እንደተመረቅሁ በአርባምንጭ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም ተመድቤ ለ7 ዓመታት አገልግያለሁ። የማስትርስ ዲግሪዬን እንደጨርስሁ በወቅቱ በጓደኞቼ ዘንድ ይወራ የነበረው መንግስታዊ ባለሆኑ ድርጅቶች መቀጠር ከፍተኛ ደመወዝ ያስገኛል የሚል ስለነበረ እኔም በአንድ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ተወዳድሬ በሥራ አሥኪያጅነት ለአንድ ዓመት አገልግያለሁ። እንደተባለው ወፍራም ደመወዝ፣ ምቹ ቢሮና መኪና የተሰጠኝ ቢሆንም በሥራየ ደስተኛ ስላልነበርኩ ከግማሽ በላይ ደመወዝ በመቀነስ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት ተቀጥሬ እስከአሁን ድረስ በደስታና በእርካታ በማገልገል ላይ እገኛለሁ።

ናይል፡- በአሁኑ ሰዓት አዲስ ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው ወደ ዩኒቨርስቲ የገቡበት እንዲሁም ትምህርት የጀመሩበት ሰዓት ነው። በመሆኑም ከእርስዎ ልምድ በመነሳት ምን ይመክሯቸዋል?

ዶ/ር ዓለማየሁ፡- አዲስ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲመጡ በርካታ ጥንቃቄዎች ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ በፊት በአብዘኛው በወላጆቻቸው ክትትል፣ ቁጥጥርና ሙሉ እገዛ ሥር ስለነበሩ ወደ ዩኒቨርሲቲ በሚገቡበት ወቅት ሁሉንም ነገር በራሳቸው ውሳኔ ብቻ የሚያከናውኑ በመሆኑ ከፍተኛ ደስታ ይሰማቸዋል። ነገር ግን በነፃነት ሲወስኑ አሥፈላጊ የሆኑ የህይወት ተሞክሮዎቻቸው ገና ያልዳበሩ በመሆኑ የሚገኙበት ዕድሜም ጥናቃቄ የሚያሻው በመሆኑ ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋቸዋል። ስለዩኒቨርሲቲ ትምህርት የተሰጣቸው መረጃ የተጋነነ ሊሆን ስለሚችል መምህሮቻቸውና አማካሪዎቻቸውን በማማከር ተገቢውን መረጃ ማግኘት ይችላሉ። የመጀመሪያውን ወሰነ ትምህርት ሙሉ ጊዜአቸውን ለትምህርታቸው ብቻ ማዋል ይጠበቅባቸዋል። ዩኒቨርሲቲ ትንሿ ኢትዮጵያ በመሆኑ የተለያዩ ባህል፣ ወግ፣ ቋንቋና፣ ሐይማኖት ያላቸው ተማሪዎች የሚሰበሰቡበት በመሆኑ አንዱ ከአንዱ ባህል ለመማማርና ተከባብሮ ለመኖር ዝግጁ መሆን አለባቸው። የሚከሰቱ ጥቃቅን ሥተቶች ቢፈጠሩ እንኳ በተሞክሮ ማነስ መሆኑን ተረድተው በመቻቻልና በመወያየት ችግሮቻቸውን ለመፍታት መዘጋጀት አለባቸው። ሴት ተማሪዎች ከአላስፈላጊ እርግዝናና ከተላላፊ በሽታዎች ራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው። ሁሉም በወቅቱ የሚደርስ መሆኑን ተገንዝበው ቅድሚያ ለሚሰጠው ትኩረት በመስጠት የመጡበትን ዓላማ ከግብ ማድረስ አለባቸው። በሰዎች መካከል ያለው ልዩነት በተለይም በትምህርት ውጤት የሚታየው ልዩነት የጥረት ልዩነት እንጅ የችሎታ ልዩነት አለመሆኑን ተረድተው የሚያስፈልገው ጊዜ ለትምህርታቸው ማዋል



ይጠበቅባቸዋል።

ናይል፡- የአካዳሚክና ምርምር ልምድዎትን ቢያካፍሉን?

ዶ/ር ዓለማየሁ፡- በመጀመሪያ እያንዳንዱ የትምህርት ዘርፍ ዕውቀትና ክህሎት የተገነባው የሰው ልጆች ህይወት ተሞክሮ አካል ከሆነው ከባህል፣ ከህይማኖት፣ አፈታሪክና ከተረት ተረት የቀደምት ወላጆቻችን አመለካከት እየተወሰደ በሳይንሳዊ ዘዴ በመሞከር ለጊዜው የሠራውን የሳይንስ ምርምር ውጤቱ በማለት በየትምህርት ዘርፍና እርከኑ በማዋቀር፤ በማደራጀትና በመከፋፈል የተዘጋጀ ነው። ይህ ማለት እያንዳንዱ አካዳሚክ ዕውቀትና ክህሎት የምርምር ውጤት ነው ማለት ነው።

እኔ ምርምር የጀመርሁት ገና የመጀመሪያ ዲግሪዬን ይዤ አርባ ምንጭ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ሳስተምር በነበረበት ወቅት ነው። በዚህም የምርምር ውጤት ከደቡብ ህዝቦች ክልልና ከመምህራን ማህበር የሰርተፊኬትና የገንዘብ ሽልማት አግኝቻለሁ። ከዚያ በኋላ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት ከተቀጠርሁ በኋላ የምርምር ሥራዎችን ሠርቼ ለረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ አመልክቼ ሁሉንም የግምገማ ሂደቶች አልፎ መጨረሻ ላይ በማላውቀው ምክንያት ወደ ውጭ አገር ለትምህርት ሄዷል በሚል ተሰርዞብኛል።

የተጠናከረ የምርምር ሥራ ውስጥ የገባሁት የPhD ትምህርቴን ካጠናቀቅሁ በኋላ ነው። በድምሩ ወደ 33 የምርምር ሥራዎችን የሠራሁ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 21 በአገር ውስጥና በውጭ አገር ታዋቂ ጆርናሎች ታትመዋል፡፡ ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ከሦስት ያለነሱ የምርምር ፕሮጀክቶችን ለትምህርት ሚኒስቴር ሠርቻለሁ። ለአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ሁለት ትልልቅ የምርምር ፕሮጀክቶች ሠርቻለሁ። ለሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና ለአማራ ብሔራዊ ክልል ሴቶች ጉዳይ ቢሮ የምርምር ፕሮጀክቶች ሠርቻለሁ። ለኢንተር-አፍሪካ ግሩፕና ለአማራ ክልል ምክር ቤት “ስርዓተ-ጾታን አካቶ መሥራት” በሚል ርዕስ ምርምር ሰርቻለሁ። የምርምር

⇨

# እንግዳችን ...

ሥራዎች በአብዛኛው የሚያተኩሩት በፖሊሲ አተገባበር፣ በሒሳብና ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት፣ በብዝኃነት አተገባበር፣ በትምህርት የፆታ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት፣ በመምህርነት ሙያ፣ በሥርዓተ ትምህርት ይዘት፣ አደረጃጀትና አወቃቀር ዙርያ ነው፡፡

**ናይል፡- በእርስዎ እይታ በምርምር ዘርፍ ያልተዳሰሱ ናቸው የሚሏቸው ጉዳዮች ካሉና በቀጣይ ከእርስዎም ሆነ ከሌሎች ምሁራንና ተመራማሪዎች ምን ይጠበቃል?**

ዶ/ር ዓለማየሁ፡- እስከ አሁን ድረስ በምርምር ያልተዳሰሱ ጉዳዩች ብዙም አይኖሩም፡፡ ነገር ግን የኛ ምርምሮች ማተኮር ያለባቸው አዳዲስ ቴክኖሎጅዎች፤ ፅንስ ሀሳቦች ፣ፖሊሲዎችና አዳዲስ ሀሳቦች በተወሰነ ጊዜና ቦታ እንዴት በቀላሉ ሊተገበሩ ይችላሉ በሚለው ዙርያ እና እንዴት ውጤትን ማስመዝገብ እንችላለን በሚል ዙሪያ መሆን አለበት፡፡ ሌላው የምርምር አጀንዳ መሆን ያለበት በኛ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ እምቅ ተሞክሮዎችን መዝዞ አውጥቶና ሳይንሳዊ በሆነ መልክ አደራጅቶ በጥቅም ላይ ማዋል መሆን አለበት፡፡

በትምህርት ዘርፍ በአሁኑ ወቅት የትምህርት ጥራት የመንግስት፣ የባለሙያውና፣ የማህበረሰቡ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም በላይ የትምህርት ጥራት በአሁኑ ወቅት የሁሉም አገራት አጀንዳ ነው፡፡ የትምህርት ጥራት ምንም እንኳ አለም አቀፋዊና የፍልስፍና ምላሽ የሚሻ ጉዳይ ቢሆንም በመምህራን ሥልጠና፣ በሥርዓት ትምህርት፣ አደረጃጀትና አወቃቀር የእያንዳንዱን ትምህርትን ይዘት በማስተማር ዘዴ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ምርምር ሊሠራ ይገባል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

**ናይል፡- የማይረሱት የሕይዎት ወይም የሥራ ፈተና ካለ?**

ዶ/ር ዓለማየሁ፡- አንደኛው ለረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ አመልክቼ የተሰረዘብኝ ምክንያታዊ አይደለም በሚል ቅር ብሎኛል፡፡ ሌለው ግን የPhD ትምህርቴን አጠናቅቄ ሙሉ ጊዜዬን በምርምርና በፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት ሰጥቼ በምሰራበት ወቅት ከፍተኛ የጤና ችግር ማለትም የአንገት አጥንት ስብራት ገጥሞኝ ከህመሙ ባሻገር ተስፋ መቁረጥ አጋጥሞኝ ነበር፡፡ በተለይም ዝቅ ብሎ ለማንበብ አያስችለኝም በሚል ከፍተኛ የመንፈስ ጭንቀት ፈጥሮብኝ ነበር፡፡ አሁን በእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ ጤነኛ ነኝ፡፡

**ናይል፡- በዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሠርተዋል፡፡ በምን በምን ክፍሎችና ኃላፊነቶች ላይ ሰርተዋል?**

ዶ/ር ዓለማየሁ፡- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በአብዛኛው ያሳለፍኩት በሀላፊነት ቦታ ነው፡፡ በመጀመርያ የርቀት ትምህርት ሲቋቋም አስተባባሪ በመሆን ለሁለት ዓመት አገልግያለሁ፡፡ ከዚያም የዩኒቨርሲቲው ፕላኒንግ ኦፊሰር በመሆን በርካታ ሥራዎችን ሠርቻለሁ፡፡ የዩኒቨርሲቲው የ20 ዓመት ዕቅድ ከማዘጋጀት ጀምሮ የአሰራር ሥርዓቶች፣ የክትትልና የቁጥጥር ፎርማቶችን፣ የዕቅድና የሪፖርት አዘገጃጀት ፎርሞችን በማዘጋጀት ለየሥራ ክፍሉ እንዲተገበሩ ሠርቻለሁ፡፡ በዚህ የኃላፊነት ጊዜ የዩኒቨርሲቲው መምህራን ቁጥር 223 ነበር፡፡ ከቀድሞ የትምህርት ሚኒስተር ከነበሩት አምባሳደር ዶ/ር ገነት ዘውዴ ሀላፊነቱ ለእኔና ለዶ/ር ፀሐይ በመስጠቱ በአንድ ዓመት 250 ተጨማሪ መምህራን እንዲቀጠሩ የበኩሌን ድርሻ ተወጥቻለሁ፡፡ ከነባር ግቢዎች፣ ከማሪታይም አካዳሚና አሁን ሆስፒታሉ ከሚሠራበት ግቢ በስተቀር ሌሎች ካምፓሶች በእኔ ጥረት የተገኙ ቦታዎች ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት የተከፈቱ ፋኩሊቲዎች፣ ኮሌጆች እና የምርምር ተቋም በዚያን ወቅት በአብዛኛው የ20 ዓመት ዕቅድ ሲዘጋጅ የተካተቱ ነበሩ፡፡

ከዚህ በኋላ የPhD ትምህርቴን አጠናቅቄ ስመለስ ወዲያውኑ የተማሪዎች ዲን በመሆን አገልግያለሁ፡፡ በዚያም ወቅት የተማሪዎች አገልግሎት የሥራ ሂደት Business Process Engineering ያዘጋጀሁት እኔ ነኝ፡፡ ከተወሰኑ ተግባራት በስተቀር ሌላው በተግባር ላይ ውሏል፡፡ ከዚያም የማህበረሰብ አገልግሎት ኤክስፐርት በመሆን ቢሮውን በማቋቋም ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት አገልግያለሁ፡፡ በመቀጠል የዩኒቨርሲቲው የፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን በማገልገል ላይ እያለሁ የጤና ችግር ስለአጋጠመኝ ኃላፊነቱን ለቅቂያለሁ፡፡ አሁን የዩኒቨርሲቲው የድህረ ምረቃ ዲን ሆኜ በማገልገል ላይ እገኛለሁ፡፡

**ናይል፡- አሁን የዩኒቨርሲቲው ድህረ ምረቃ ጥናት ጽ/ቤት ዲን ሆነው እየሠሩ ነው፡፡ ስመሆኑ የድህረ ምረቃ ዘርፉ በዩኒቨርሲቲያችን ራዕይ ምን አይነት ቦታ ይይዛል?**

ዶ/ር ዓለማየሁ፡- በአሁኑ ወቅት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ግልፅ ራዕይ ነድፎ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ይህም በ10 ዓመት ውስጥ በአፍሪካ ከሚገኙ ምርጥ የምርምር ተቋማት አንዱ ለመሆን የሚል ነው፡፡ ይህንን ራዕይ በማስረጽ በኩል የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ የተጫወቱት ሚና እጅግ የላቀ ነው፡፡ አንድ ቀን ቢሮአቸው ጠርተው የዩኒቨርሲቲውን ራዕይ ለማሳካት የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት ቁልፍ ተግባር መሆኑን ገልፀውልኝ ለዚህም የበኩሌን ድርሻ እንድወጣ ጠየቁኝ፡፡ እኔም የተሰጠኝ ኃላፊነት ከባድ መሆኑን ብገነዘብም የፕሬዚዳንቱ ፍላጎትና ጥረት ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ ኃላፊነቱን ተቀብያለሁ፡፡

አንድ ዩኒቨርሲቲ የምርምር ተቋም ለመሆን፡- በዓመት ከ100 ያላነሱ PhD ምሩቃን ሊኖሩት ይገባል፣ መምህራንና ተማሪዎች በምርምር ሥራ የሚሳተፉና በታዋቂ ጆርናሎች የሚያሳትሙ መሆን አለባቸው፤ በተጨማሪ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ኮንፍረንስ የምርምር ሥራዎቻቸውን ማቅረብ፣ በአብዛኛው መምህር የPhD ምሩቅ መሆን ይጠበቃል፣ መምህራንና ተማሪዎች በአገር ውስጥና ውጭ አገር ፕሮጀክቶችን ተወዳድረው ማሸነፍ እና የመምህራንና ተማሪዎች የሚሰሩቸው ምርምሮችና የቴክኖሎጅ ውጤቶች ወደ ገንዘብ (ቢዝነስ) ተቀይረው በማህበረሰቡ ዘንድ ለውጥ ማምጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች መሥፈርቶችን ያሟላ ተቋም የምርምር ተቋም ይባላል፡፡ ከዚህ አንፃር የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት በተለይም የPhD ፕሮግራሞችን ማስፋፋት የመምህራንና የተማሪዎችን የምርምር አቅም ከማጎልበት አኳያ ሲታይ የማይተካ ድርሻ አለው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲገመገም ምንም እንኳ ራዕይውን ለማሳካት የበላይ አመራሩ ሚና እና የሁሉም ዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ርብርብ ወሳኝ ቢሆንም የድህረ ምረቃ ጽ/ቤት ስትራቴጅዎችን በማስፈፀም በኩል ከፍተኛ ኃላፊነትና ድርሻ ይጠበቅበታል፡፡

እኔ ኃላፊነቱን ስረከብ አራት የPhD ፕሮግራሞች ብቻ ነበሩ፡፡ በአሁኑ ወቅት 28 PhD ፕሮግራሞች ሥርዓት ትምህርታቸው ተጠናቆ ከጥቂቶቹ በስተቀር ተማሪ ተቀብለው በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡፡ የታቀደው በሙሉ ከተሳካ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የPhD ፕሮግራሞች ቁጥር ወደ 60 ከፍ ይላል፡፡ እነዚህ ፕሮግራሞች በሙሉ ተማሪ ተቀበለው ማስመረቅ ሲጀምሩ የዩኒቨርሲቲውን ራዕይ ለማሳካት ረጅም ረቀት መጓዝ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሚከፈቱ PhD ፕሮግራሞች የዩኒቨርሲቲው መምህራን ገብተው እንዲማሩ ይጠበቃል፡፡ ይህም ከፍተኛ ለሆነ የመምህራን ልማትን ከማሳካት አኳያ አስተዋጽኦ ያበርክታል፡፡ በዚህ ምክንያት የመምህራንና የተማሪዎች የምርምር አቅም ይጐለብታል፡፡

**ናይል፡- ስድህረ ምረቃው ዘርፍ መሳካት ሌሎች ተባባሪ አካላት (ፕሬዚዳንቶች፣ ዲኖችና ዳይሬክተሮች) ሊያደርጉ የሚገባቸው ነገሮች ካሉ ቢገልጹልን?**

ዶ/ር ዓለማየሁ፡- ከዚህ አንፃር ሲታይ የዩኒቨርሲቲውን ራዕይ ለማሳካት የድህረ ምረቃ ጽ/ቤቱ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳን የድህረ ምረቃ ጽ/ቤት በቀጥታ ስትራቴጅዎችን ከማስፈፀም አኳያ ኃላፊነት ቢኖረውም የበላይ አመራሮች ሚና ከሁሉም የላቀ ነው፡፡ ፕሬዚዳንቱና ም/ፕሬዚዳንቶች ራዕይውን ለማሳካት አመራር በመስጠት፤ አዳዲስ ሀሳቦችን በማፍለቅና አተገባበራቸውን በመቀየስ ለድህረ ምረቃ ጽ/ቤቱ በማስተላለፍ የማይተካ ድርሻ አላቸው፡፡ ዲኖችና በተለያየ እርከን ያሉ ኃላፊዎች ስትራቴጅዎችን በመተግበር ቀጥተኛ ኃላፊነት ያላቸው በመሆኑ ያለ እነሱ ጉልህ አስተዋጽኦ የዩኒቨርሲቲው ራዕይ ሊሳካ አይችልም፡፡ ከሁሉም ባልተናነሰ ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ራዕይውን ተረድተው የየበኩላቸውን ድርሻ ካልተወጡ በስተቀር ራዕይውን ማሳካት አይቻልም፡፡

ከዚህ ጋር አያይዤ አንድ ተሞክሮዬን ማካፈል እፈልጋለሁ፡፡ የፕላኒንግ ኦፊሰር ሆኜ የ20 ዓመት ስትራቴጀክ ፕላን ሳዘጋጅ የሚሰጠኝ ትችቶች ነበሩ፡፡ የአንድ ዓመት ዕቅድ መፈፀም አቅቶን የ20 ዓመት ታወራለህ፡፡ ይህ ሁሉ አይፈፀምም የሚል ትችት ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን ላይ ቆሜ ሳየው በአብዛኛው የ20 ዓመት ዕቅድ ተፈፅሟል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ራዕይ በወቅቱ ማየት እንደምንችል አምነን የበኩላችንን ድርሻ እንድንወጣ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የድህረምረቃ ፕሮግራሞች መስፋፋት አገሪቱ የተያያዘችውን ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ከማሳካት አኳያ ጉልህ አስትዋጽኦ አለው፡፡ በዚህም እቅድ ግብርናው መሪነቱን ይዞ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር በማድረግ ደረጃ በደረጃ የManufacturing እና የኢንደስትሪው ዘርፍ ልማት እድገት ቀዳሚነቱን እንዲይዝ በማለም ነው፡፡ በዚህ በኩል በርካታ ተመራማሪዎችን በግብርናው፤ በጤናው፤ በቴክኖሎጅው፤ በትምህርትና በሌሎች መስኮች ማፍራት፡ ቴክኖሎጅን በመጠቀም፤ ቀልጣፋና አዳዲስ አሰራሮችን በማስፈን ምርትና ምርታማነትን በየዘርፉ በምርምር የሚያሳድጉ ባለሙያዎችን በስፋት ለማግኘት ያስችላል፡፡ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠኑ ባለሙየዎችን ማፍራት በወቅቱ በመስፋፋት ላይ ላሉ እና አዲስ በመከፈት ላይ ላሉ ዩኒቨርሲቲዎች የሰለጠነ ባለሙያ በማቅረብ ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት ጥራት ያለው ባለሙያ ለማፍራት ያስችላል፡፡

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# ገጠመኝ ...

ከገጽ 7 የዞረ

መመሪያ ሰጥቻለሁ፡፡ ጊዜው ረጅም በመሆኑ ያለውን ሁኔታ ግን መናገር ይከብደኛል፡፡ ምናልባት እነዚህ የኔ ተከታይ ሹማምንቶቼ ታች እንዳይደርሱ አድርገው በማቆየታቸው ያባባሰባቸው ነገር እንዳይኖር'' አለ አፉ እንደመያያዝ እያለ፡፡

መርማሪዎቹ ተያዩና ተግባቦት ወደ ገባችበት ክፍል እንዲገባ አዘውት ቀጣይ ተረኛዋን ቡድኔን አስገቧት፡፡ የወ/ሮ ቡድኔ መልስ ከሌሎች ለየት ያለ ነበር፡፡ ከአቶ ለውጤ ሞት ጋር ያልተያያዘና መርማሪዎቹንም ፈገግ ያሰኘ ነበር፡፡

''እኛ ቡድን የምንባደነው ለማህበራዊ ኑሯችን ስንል ነው፡፡ ስንት ነገር አለ በሰው ላይ'' አለች ገና ስትጀምር፡፡ መርማሪዎቹ ለጥያቄ ጊዜ ስላልሰጠቻቸው እያዩ ዝም አሏት፡፡ ቀጠለች እሷ ''ሰው ሲታመም፣ ሲወልድ፣ ሲያገባ፣ ቤት ሲሰራ፣ ሲመረቅ፣ እንደው ብቻ በደስታና በሃዘን አንዳንዴም ሰበብ ፈልገን የምንጠያየቅበት መድረክ ነው ያለን'' አለች፡፡ ''ደግሞ እኮ አቶ ለውጤ ማህበራዊ ኑሮ አያውቅ፤ ቢቀላቀለን ኖሮ ተመላልሰን እንጠይቀው እንዲያውም ከሞቱም እንታደገው ነበር፡፡ እሱ ሥራ ጠም በመሆኑ ሁሌ ተቸክሎ ይኸው ሞተና አረፈው፡፡ እና እኔ ታዲያ አቶ ለውጤን በቅጡ እንኳ ሳልተዋወቅ ምን ፍጠሪ እባላለሁ''? ብላ ለክርስትና የያዘቻትን የመዋጮ ወረቀት ለአቶ ትጋት ቀስ ብላ አቀብላ በነበረችበት ቦታ ቆመች፡፡ ተፈቅዶላት ከአቶ ትጋት ጎን ተቀመጠች፡፡ በመቀጠል ፈጠኑ ተጠርታ ገባችና ጥያቄው ቀጠለ፡፡ ወ/ሮ ፈጠኑ ነገሯ ሁሉ እንደስሟ ፈጣን ሲሆን ስትመልስ ''ባካችሁ ተውኝ ማን ይሰማል እንጂ፤ እኔ'ኮ አቶ ለውጤ እንደሚሞቱ ቀድሜ ተናግሬ ነበር፡፡'' አለች በቁጭት፡፡

''ስብሰባ አዳራሽ ቁጭ ብሎ መቀመጫ በማሸት የአቶ ለውጤን እድሜን መቀጠል የሚቻል ይመስላችኋልን? ሁሉ ተቀምጦ ሲያወድሳቸው ቢውል ምን ይጠቅማቸዋል፡፡ ተነስቶ እጅጌውን ሰብሰብ አድርጎ ካልሰራላቸው በስተቀር፡፡ ያለንን ይዘን ብንሟሟት፣ ብንፈጥን፣ ጤናቸው መታወክ ሲጀምር ነቃ ብለን ጠየቁና አመኑን አጥብቀው እንዲያግዟቸው ብናደርግ ኖሮ ዛሬ ታሪኩ ሌላ ይሆን ነበር፡፡ ውዳሴ ሆድ ይሞላል፣ በሽታ ይፈውሳል? ይልቅስ አታስቁኝ፤ እናንተ ደግሞ አበስብሳችኂቸው ሌላ ምርመራ እንዳተስጠሩብኝ'' ብላ እየተቆናጠረች መለስ ብላ አንኳ ሳታያቸው ወጥታ ሄደች፡፡

አመኑና ጠየቀ ውጭ መጠበቁ ሰልችቷቸው ፈጠኑ እንደወጣች ማንም ሳይጠራቸው ተንደርድረው አብረው ገቡና ሁለቱም በአንዴ ማውራት ጀመሩ፡፡ ''እኛ የዚህ ቤት የእንጀራ ልጆች ነን፣ ሁሉ የሚሸነግለን ትርፍ ነን፣ መርማሪዎች እባካችሁ አሁንም ቶሎ አንድ በሉ፡፡ ያለበለዚያ የዚህ መስሪያቤት ቀንድ የሆኑት እነትጋትም መሰናበታቸው የማይቀር ነው፡፡ በኛ በአመራሮቹ መካከል ራሱ ተማምኖና ተመካክሮ መሥራት ይጎድላል፣ መከፋፈል አለ፡፡ ማንም ይህን አይልም እንጂ፡፡ ከሥራው ይልቅ ለፕሮቶኮሉ ጊዜ ገንዘብና የሠው ኃይል ተመድቦ ሁሌም ድግስ ላይ ነው ያለነው!''

አቶ ጠየቀ እንደመሰላቸት ብሎ ዝም ሲል ወ/ሮ አመኑ ግን አልተወጣላቸው ነበር፡፡ ''የኔን ሥራ በጉዝጓዝና ጭሳጭስ በይስሙላ ስብሰባና ግምገማ ሰውን ማሰላቸት አድርገው የሚያዩት ብዙዎች ናቸው፡፡ ይመስላችኂል? አይደለም፡፡ ልቅም አድርጎ ሰው በሚገባው ቋንቋ መንገርና በተግባር እየተከተሉ መደገፍ ሙያ ሲጎድል መሙያ ብልሃቱን ማከል የሚጠይቅ ነበር፡፡ ታዲያ ያደክማልና ማን የኔ አቻና አለቃ ይደፍራታል? እናም አቶ ለውጤ መዳን መኖር እየቻሉ ላግዛቸው ሲገባኝ እጅ ከወርች ታስሬ ሲሞቱ ቆሜ አየሁ፡፡'' እያሉ ውርጅብኛቸውን አዥጎደጎዱት፡፡ ሁለቱም ያነሱት ነገር ከአቶ ምራው ጋር ስለተያያዘ አቶ ምራው ዳግም ተጠራና ለነዚህ ወገኖች ተገቢው ሥራ እየተሰጣቸው ስለመቆየቱ ተጠየቀ፡፡ ከረባቱን እያስተካከለ እርግጥ ጉዳይ ሲኖር ወደነሱ እንልካለን፡፡ አብረውም እንዲሠሩ እናደርጋለን፡፡ ሆኖም አቶ ጠየቀ በሥራ ስምሪት ውስጥ ስናስገባው ግጭት እየተፈጠረ ስለምንቸገር ተጠንቅቀን ለማስኬድ ነው የምንሞክረው፡፡ ተሹሞ ስለመጣ እንጂ እኛ ጥያቄ አቅርበን የመጣም አይደለም፡፡ ወ/ሮ አመኑ ተሰጥቷቸው የሚሠሩትና በጋራ ስናሰራቸውም ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ ደፍረን በሳቸው ፍጥነት መራመድ አልፈለግንም፡፡ እርግጥ እነሱ አሁን ሲናገሩ ከሰማሁት እንደተረዳሁት ሁለቱን በመጠኑ እንኳ ተጠቅመን ቢሆን ኖሮ ሟቹን እንታደጋቸው እንደነበር ነው'' አለ አቀርቅሮ፡፡

መርማሪዎቹ ደከማቸውና ሁሉንም ወደየቤታቸው እንዲሄዱ ፈቅደው ሊወጡ ሲሉ የአቶ ለውጤ የአስከሬን ምርመራ ውጤት የያዘ ሃኪም በር ላይ አቆማቸው፡፡ እናም እንደገና ወደቢሮ ተመልሰው ውጤቱን በጋራ ማየት ጀመሩ፡፡

በሃኪም ቤቱ ባለአርማ ወረቀት ላይ ብዙ ሃተታ ቢኖርም መርማሪዎቹ የሚከተሉትን ነጥቦች በማስታወሻቸው ላይ አሰፈሩ፡፡

> ሙሉ ስም ለውጤ ቢኖር ታድጎ፣ ዕድሜ 48 (ወር ይሆን?)፣
>
> የምርመራ ምክንያት የሞት መንስኤ ምርመራ፣ ምርመራው የተከናወነበት ቀን 12/12/12
>
> የምርመራ ውጤት፡-
>
> ''ሟቹን ለዚህ ፍፃሜ ያደረሳቸው በድርጅቱ ውስጥ ያሉ ኃላፊዎች ያለማሰለስ ሲሰጧቸው የቆዩት ማረሳሳትና መዘንጋት የሚባሉ የአመራር ህይወት ማሳለጫ መድሃኒቶች ጫና ሲሆን ጫናው ወደሞት እንዳይወስዳቸው እንዲከታተሉ ቀደም ሲል ስልጠና ተሰጥቷቸው ተመድበው የነበሩት ፈጠኑ፣ ጠየቁና አመኑ የተሰጣቸውን ሥራ ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጽሙ ተደረጎ ሊሆን እንደሚችል የሃኪሞች ቦርድ ያምናል፡፡'' ይላል ሰነዱ፡፡ መርማሪዎቹ ተያይዘው ወጡ፡፡

እኔም የአዲሱ መስሪያ ቤት የመጀመሪያ ውሎዬ ይኸው ሁኖ ጧት ይዣት የወጣኂትን ቦርሳ እንዳንጠለጠልኩ እቤት ገባሁ፡፡

ማስታወሻ ስለባለታሪኮቹ

1. አቶ ለውጤ - Institutional change
2. አቶ ምራው - Leadership
3. ወ/ሮ ቡድኔ - Team spirit
4. ወ/ሮ ፈጠኑ - Urgency
5. አቶ ትጋት - Commitment
6. ወ/ት ተግባቦት - Communication
7. አቶ ጠየቁ - Accountability
8. ወ/ሮ አመኑ - Consensus Building

# የግጥም ጥግ

## ውጡ ከኢትዮጵያ

የአለባበስ ባህል ፀጉር ያስከፋችሁ፣
ባለጤና ሰዎች እብድ ያስመሰላችሁ፡፡
አልኮልና ዝሙት ጫት ሲጋራ አብራችሁ፣
መሰልጠን መስሏችሁ የደነቆራችሁ፣
ባህል ክስ አቅርቧል ውጡልን እባካችሁ፡፡

እናንተም አስቡ ሰው ትልቅ ፍጡር ነው፣
ከባህል ከሥርዓት ማፈንገጥ ወንጀል ነው፣
ይግባኝ ሰሚም አይኖር ለእድሜ ልክ እስር ነው፣
በአዋጅ እስኪነገር ማሰቡ መልካም ነው፡፡
አባቶች እናቶች ወንድሞች እህቶች፣

መምህራን በሙሉ የቀለም አባቶች፣
ቀሣውስት ዲያቆናት የሐይማኖት ሰዎች፣
ፀጥታ አስከባሪ ፖሊስ እና ዳኞች፣
ምከሩ አስተምሩ አንሁን አመልካቾች፣
ባህል ይወቅሰናል ልጆች የልጅ ልጆች፡፡

ከ፲ ሞላ መስፍን
ከባሕር ዳር ኗሪ

# ስብሰባው (አጭር ልቦለድ)

በደስታ ተክስተ
ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፀጥታ አገልግሎት

የምሽቱን ዜና ስታደምጥ ቆይታ ከዜናዎቹ መካከል ስለምትሰራበት መስሪያ ቤት የተነገረው አበሳጭቷታል። «እንዴት አንድ ሚዲያ እንዲህ ያለ ዘገባ ያሰማል?... ቢያንስ... ቢያንስ በቦታው የነበሩ ሰዎች ይታዘባሉ ብለው አያስቡም እንዴ?» እያለች ትብከነከናለች ጉዳዩን በአስተያየት መልክ ለጣቢያው ለማሳወቅ ሞባይሏን ካስቀመጠችበት ጠረጴዛ ላይ አንስታ ቁጥሮችን ነካክታ ደወለች፣ «ተይዟል» የሚል ድምፅ አሰማት ደጋግማ ሞከረች አልገባላትም የዜናው ሀሳብና በወቅቱ በስብሰባው ላይ የነበረው ሁኔታ እያስገረማት ማስታወሻዋን ከቦርሳዋ ውስጥ አውጥታ የዕለቱን ስብሰባ ገጠመ▯ን ገፅ በገፅ እያገላበጠች ለግሏ ማንበብ ጀመረች።

* * *

በተቋሙ ውስጥ ያለው የመሰብሰቢያ አዳራሽ በባንዲራዎች ደምቋል በአዳራሹ መግቢያ በር ላይ «ውድ ተሰብሳቢዎቻችን እንኳን በደህና መጣችሁ» የሚል ፅሁፍ ተፅፎ ተሰቅሏል ወደ ውስጥ ሲዘልቁ ከዝቅተኛ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች እስከ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ገብተው አዳራሹን ሞልተውታል።

ፊት ለፊት በመድረኩ ላይ ሶስት የስብሰባ መሪዎች ተሰይመዋል። መሀል ላይ የሚታዩት የመስሪያ ቤቱ ኃላፊ ናቸው። ስብሰባውን በዋናነት የሚመሩት እርሳቸው ናቸው። «ድህነት በሥራ ይሸነፋል» የሚል ፅሁፍ ያለበት ባነር በመድረኩ ጀርባ ግድግዳ ላይ ፊት ለፊት ተሰቅሎ ይታያል። በአዳራሹ ግራና ቀኝ ግድግዳ ላይ ደግሞ በነጭ አቡጀዴ ላይ የተፃፉ የተለያዩ መልዕክቶች ይነበባሉ በስተቀኝ በኩል ያለው፣ «በሰራተኞቻችን አቅምና ጠንካራ የስራ ባህል የመስሪያ ቤታችን ራዕይ እውን ይሆናል» የሚል ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ በግራ በኩል ያለው ፅሁፍ፣ "የሀገራችን ትልቁ ጠላት ድህነት ነው!! ድህነትን ለማጥፋት የበኩሌን ድርሻ እወጣለሁ እናንተስ?" የሚል ነው። በአዳራሹ ባሉት ሁለት ቋሚዎች ላይ ተወጥሮ የተሰቀለው ሌላው ፅሁፍ፣ «ውድ ተሰብሳቢዎቻችን እናንተ በምታደርጉት የነቃ ተሳትፎ ስብሰባችን ግቡን ይመታል» ይላል።

ስብሰባው ይጀመራል በተባለበት ሰዓት አልተጀመረም ሰዎች በመሰላቸት እርስ በርሳቸው ይነጋገራሉ። ጥቂቶች በተቀመጡበት በእንቅልፍ መንፈስ ያንጐላጃሉ አንዳንዶች በያዙት ሞባይል ኢንተርኔት ከፍተው ያያሉ ሌሎች አጠገባቸው ካለው ሰው ጋር የጦፈ ወሬ ይዘው ያውካካሉ ስብሰባው እስኪጀመር አዳራሹ የደራ ገበያ አይነት ድምፅ ይሰማበታል።

ከተሰብሳቢው መካከል የተላከች ብጣሽ የተጠቀለለች ወረቀት በሰብሳቢው እጅ ገባች ኃላፊው ወረቀቷን በጥንቃቄ ገልጠው አነበቧት «እባካችሁ ስብሰባውን አስጀምሩንና በሰዓቱ እንጨርስ» የሚል መልዕክት ይዛለች። ወዲያው ሞባይላቸውን አውጥተው ደወሉ። የሚሉት ለተሰብሳቢው ባይሰማም ልክ እንደጨረሱ መነጋገሪያውን አንስተው "ይቅርታ የተከበራችሁ ተሰብሳቢዎቻችን ስብሰባችንን በሰዓቱ ያልተጀመረው 'የሚዲያ' ሰዎችን እየጠበቅን ስለሆነ ነው የዛሬው ስብሰባችን በቴሌቪዥንና በራዲዮ ስለሚነገር ትንሽ ታገሱን ባይሆን እስከዚያው የስብሰባው አስተባባሪዎች እሽግ ውሃ እንዲያድሏችሁ እናደርጋለን" ብለው ሲጨርሱ ሞቅ ያለ የተሰብሳቢው ጭብጨባና ፉጨት አጀባቸው።

ወዲያው ለእያንዳንዱ ተሰብሳቢ ውሃ መታደል ተጀመረ በዚህ ጊዜ ታዲያ ውስጥ ለውስጥ በሹክሹክታ ቀልድ ተጀመረ "እንዴ ጋዜጠኞች ሳይመጡ መጠጣት የለብንም። ውሃው ሲታደለንና ስንጠጣ በቴሌቪዥን መታየት በሬድዮም መሰማት አለበት። በኋላ ጋዜጠኞቹ ሊታዘቡ ይችላሉ እኮ!" «እረ ተውኝ እኔ ለራሴ ጠምቶኛል? ማታ ትንሽ ሥራ በዝቶብኝ ነው ያደርኩት።» የሚሉ የቀልድ ሀሳቦች ከአንዳንዶች ተሰምተው ነበር። ውሃው ታድሎ እንዳበቃ በመድረኩ ላይ ተቀምጠው የነበሩት ሶስት ሰዎች ብድግ አሉ። መነጋገሪያውን የያዙት የስብሰባው መሪ «ውድ ተሰብሳቢዎቻችን የምንወዳቸውና የምናደንቃቸው እንዲሁም የምናከብራቸው የቴሌቪዥንና የሌሎች ሚዲያ ጋዜጠኞቻችን ወደ ስብሰባ አዳራሹ እየገቡ ስለሆነ ተነስተን በጭብጨባ እንድንቀበላቸው በአክብሮት አሳስባለሁ» ከማለታቸው ሁሉም ተሰብሳቢ በማጨብጨብና በማፏጨት ለጋዜጠኞቹ አቀባበል ተደረገላቸው። ኃላፊውም "የተከበራችሁ ተሰብሳቢዎቻችን ለጋዜጠኞቻችን ስላደረጋችሁልን ደማቅ አቀባበል በራሴና በማንጅመንቱ ስም አመሰግናለሁ። ተቀመጡ እግዜር ያክብርልን" አሉና እርሳቸውና አብረዋቸው ያሉት ሲቀመጡ ተሰብሳቢውም በደማቁ አጨብጭቦ ተቀመጡ።

ጋዜጠኞቹ ካሜራቸውንና መቅረፀ ድምፃቸውን እስኪያስተካክሉ ጥቂት ደቂቃዎችን አጠፉ። የስብሰባው መሪ የሆኑት የመስሪያ ቤቱ ኃላፊ ንግግር ማድረግ ጀመሩ። «የተከበራችሁ የመስሪያ ቤታችን የልዩ ልዩ የሥራ ክፍል ኃላፊዎችና መላው ሰራተኞቻችን፣ ተቋማችን በሚያካሄደው አመታዊ ስብሰባ ላይ ጥሪያችንን አክብራችሁ በመገኘታችሁ በተቋሙ ማንጅመንት ስም ላመሰግን እወዳለሁ። እንኳን ደህና መጣችሁ...» እንዳሉ አዳራሹ በተሰብሳቢዎች ጭብጨባና ፉጨት ደመቀ። ኃላፊው ንግግራቸውን ቀጠሉ «የዛሬ ቀን ስብሰባችንን ለየት የሚያደርገው ጉዳይ ቢኖር በእውነቱ። የምናደንቃቸውና የምንወዳቸው የቴሌቭዥንና የሬድዮ እንዲሁም የህትመት ጋዜጠኞቻችን በተገኙበት መሆኑ ነው። ውድ ጋዜጠኞቻችን ጥሪያችንን አክብራችሁ በሰዓቱ ስለተገኛችሁልን በራሴና በዚህ ተሰብሳቢ ስም ላመሰግን እወዳለሁ...» ከማለታቸው አሁንም አዳራሹ በጭብጨባ አስተጋባ። በዚህ ጊዜ አንዳንድ ጋዜጠኞችም ወደ ተሰብሳቢው ዞረው ከአንገታቸው ጐንበስ በማለት ምላሽ ሰጡ። ሰዓቱ እየገሰገሰ ነው ዋና የስብሰባው ሀሳብ እስካሁን አልተገለጠም የተሰብሳቢው ጭብጨባ ጋብ እንዳለ ኃላፊው ቀጠሉ «የተከበራችሁ ተሰብሳቢዎቻችን አንድ ልታውቁት የሚገባ ጉዳይ ቢኖር በዛሬው ስብሰባችን ላይ እንዲገኙልን የጋበዝናቸው ጋዜጠኞች አሁን የሚታያቸውን ብቻ አልነበረም። ሌሎች የሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ሚዲያዎች የሚዘግቡትንም ጋብዘን ነበር ለምን እንዳልመጡ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም ወደፊት በሚገባ አጣርተን ለዚህ ተሰብሳቢ የምናሳውቅ መሆኑን በራሴና በማኔጅመንቱ ስም ቃል እገባለሁ» እንዳሉ ጭብጨባው አስተጋባ ኃላፊው ቀጠሉ፤ «በመሆኑም ጥሪያችንን አክብረው ለመጡት ለነዚህ ሀገር ወዳድና ልማታዊ ጋዜጠኞቻችን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት በድጋሜ ተሰብሳቢው እንዲያጨበጭብላቸው በአክብሮት እጠይቃለሁ።» ተደጋጋሚ ተሰብሳቢው ጭብጨባና ፉጨት አሰማ አንዳንድ ሴቶችም እልልታ አሰምተዋል። ጋዜጠኞች የኃላፊውን ንግግርና የተሰብሳቢውን ጭብጨባ መቅረፅ ቀጥለዋል። ሰዓቱም ይከንፋል። ዋና የመወያያ ርዕሱ አሁንም አልተነሳም።

«እሺ» አሉ ሰብሳቢው፣ «እሺ የተከበራችሁ ተሰብሳቢዎቻችን አሁን ስብሰባችንን እጀምራለን... በእለቱ የምንወያይባቸውን ጉዳዮች እንደሚከተለው አሳውቃለሁ። አንደኛ መስሪያ ቤታችን ባለፈው አመት ያስመዘገባቸውን ውጤቶች እናያለን። በሁለተኛ ደረጃ መስሪያ ቤታችን ሕዝብና መንግስት የጣሉበትን ድህነትን የመቀነስ አደራ ኃላፊነቱን እንዴት እየተወጣ ነው? ሶስተኛ የመስሪያ ቤታችንን ራዕይና ተልእኮ ከመፈፀም አንፃር የእያንዳንዳችን ሰራተኞች ሚና ምን መምሰል አለበት? እንዴትስ እየተጋን ነው? የሚሉትን ሀሳቦች አንስተን ከተወያየን በኋላ ቀሪ ጉዳዮችን ደግሞ እናያለን። የስብሰባችን አካሄድ የሚሆነው መጀመሪያ ከእናንተ ከተሰብሳቢዎቻችን በተነሱት ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ሀሳቦች ይቀርቡና ቀጥሎ ደግሞ እናንተ ባነሳችኋቸው ሀሳቦች ላይ የተለያዩ የሥራ ኃላፊዎች ማብራሪያ እንዲሰጡበት ይደረጋል...» አሉና ቀና ብለው ተሰብሳቢውን በሙሉ አይናቸው ግራ ቀኝ ተመልክተው፣ «አሁን እድሉን ለተሰብሳቢው ሰጥቻለሁ ሀሳብ ያለው እጁን አውጥቶ ያሳየኝ» ኃላፊው አይናቸውን ከወዲያ ወዲህ በተሰብሳቢው ላይ አንከራተቱ እጁን ቶሎ የሚያወጣ ሰው አልታይህ አላቸው «ምነው ጐበዝ! ግልፅ አይደለም እንዴ?» አሉ-ግራ የተጋቡ በመምሰል። ከወደ ኋላ በኩል አንድ ሰው እጁን አውጥቶ ሲያውለበልብ ታያቸው፣ «እሺ እዚያ ጋ... አዎ በኋላ በኩል መነጋገሪያውን ስጡልኝ» አለ የመናገር እድሉ የተሰጠው ሰውዬ ገመድ አልባ መነጋገሪያው እጁ እንደገባ፣ «እፍ...እፍ እሰማለሁ?» ሲል «ይሰማል ቀጥል» አሉት ሰብሳቢው «እሺ ለተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ። «ይቅርታ መጀመሪያ ስምህና የሥራ ኃላፊነትህን ጥቀስልን» አሉት ሰብሳቢው ጣልቃ በመግባት።

«እሺ ስሜ ዘብጤ መካሻ ይባላል የሥራ ኃላፊነትህ ለተባለው ያው በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ሰራተኛ ነኝ። እኔ መናገር የምፈልገው ሁለት ሀሳብ ብቻ ነው 'ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫኑም' እንደሚባለው ነገሬን በአጭሩ አቀርባለሁ። እ.እ... አንደኛ የዛሬው ስብሰባችን የውሎ አበል አለው ወይ?» የሚል ጥያቄ ሲሆን ሌላው ሀሳቤ ቅድም ጋዜጠኞቻችን እስኪመጡ ድረስ ብላችሁ የሰጣችሁን ውሃ ስላልበቃን በድጋሜ ቢታደለን

ውሃው ሲታደለንና ስንጠጣ በቴሌቪዥን መታየት በሬድዮም መሰማት አለበት። በኋላ ጋዜጠኞቹ ሊታዘቡ ይችላሉ እኮ!

ወደ ገጽ 13 ዞሯል

# ሽማግሌው 2

አትክልት ዳኛው የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ግቢ የጋይዳንስና ካውንስሊንግ ባለሙያ

(ይህ ፅሁፍ ከነሀሴ ወር እትም ላይ 'የሽማግሌው ኑረት' የሚለው ፅሁፍ ቀጣይ ክፍል ነው)

ሽማግሌው ልጆቹን በአንክሮ ተመልክተው ልጆቼ እዚህ ሀገር ስኖር ብዙ ትውልዶች እየመጡ ሂደዋል፡፡ እኔም እሄዳለሁ፡፡ አሁንም እናንተ በአዲስ ሀይል እየመጣችሁ ነው፡፡ በእናንተ ተስፋ አለኝ፡፡ ለዚህ ነው ይኸው ድመቴ እርቦት እያለ እናንተ ጋር ቆሜ የምወያይ፡፡ የኔ ልጅ ስምሽ ማንነው? «መሰረት» አሉ ብዙ ድምፆች በአንድነት፡፡ እውነትም መሰረት ስምን መላዕክ ያወጣዋል እንዲሉ፡፡ አንቺ ለብዙዎች የምትጠቅሚ የመሰረት ድንጋይ እንደምትሆኚ እምነቴ ነው፡፡ እርስዎ ትልቅ ሰውዬ ሞትን ይፈራሉ ወይ? ብለሽ የጠየቅሽኝ ጥያቄ ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ አዎ እኔ በተለምዶ ሞት ብለን የምንጠራውን አልፈራም፡፡

ነገር ግን እስትንፋስ ያላቆመበትን፣ መንቀሳቀስ ያለበትን፣ መብላት እና መጠጣት እንደህይወት ግብ የሚቆጠርበትን በሥጋ እየኖሩ በመንፈስ የሚከስሙበትን ደመነፍሳዊ ሕይወት ነው ሞት ብዬ የምጠራው እና አጥብቄ የምፈራው እንጂ በተለምዶ ነፍስ ከስጋ የምትለይበት ተፈጥሯዊ ግዴታ እንጅ ሞት ሊባል አይገባውም፡፡ በዚህ ተፈጥሯዊ ግዴታ ውስጥ የሌላው ውልደት ይፀነሳል፡፡ ለምሳሌ ስንዴን ብንወስድ በአንድ ስንዴ መቃብር የሌላ ብዙ ስንዴዎች መውለድ እውን ይሆናል፡፡ እኛም በተለምዶ «ሞት» ብለን በምንጠራው ነፍስ ከስጋ የመለየት ተፈጥሯዊ ግዴታ ለሌሎች መኖር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ እስቲ ሁሉም ሰው ህይወቱ የማታልፍ ቢሆን ኖሮ የአለም ገፅታ ምን ሊመስል እንደሚችል አስቡት? ልጆቹ በግራ መጋባት አይን ሲያዩዋቸው ሀሳቡ ረቂቅ እንደሆነባቸው ሽማግሌው ገመቱ፡፡ ከህፃናቱ መካከል ጋሻው "የሞተ ሰው ይ.. ይበላል ይእእ.. ተነፍሳል?" ብሎ ሲጠይቅ ሁሉም ልጆች በአንድነት ሳቁ፡፡ ጥያቄው አይደለም ያሳቃቸው የጋሻው ዲዳ አንደበት ሲኮላተፍ መደመጡ እንጂ፡፡ ሽማግሌውም "የኔ ልጅ እኔ እያወራሁ ያለሁት በሕይወት እየኖርን ሲሉ በመንፈስ ስለሞቱት ነው፡፡ ለምሳሌ እናንተ ቤት ስንዴ አለ?» ብለው ሲጠይቁ አዎ "አዎ" አሉ ብዙ ድምፆች፡፡

"ነቀዝ ስለሚባል ትንሽ ነፍሳትስ ካሁን በፊት ስምታችሁ ታውቁ ይሆን? ቅድም ስለስንዴ የጠየቅኋችሁ ነቀዝ ስንዴን ከአንዱ ጫፍ ትበሳውና ውስጡ ያለውን በሙሉ ትበላዋለች፡፡ ውስጡ ያለው ዱቄት ያልቅና ቀፎው ይቀራል፡፡ በደንብ አድርገን ካላጤነው መበላቱን አናውቀውም፤ በነቀዝ የተበላ ስንዴ ብንዘራው አይበቅልም፣ ለምግብነት አይውልም ያለ ሲመስለን የለም፡፡ ያው ቀይ ብቻ ነው፡፡ እና ልጆቼ ሰውም እንደ ስንዴው ሲነቅዝ ቀፎውን ስናየው ደህና ቢመስለን በሕይወት አለ እንላለን እንጅ ውስጡ ዱቄት ከሌለው ከመሞት የባሰ ነው፡፡

አንድ ህፃን ጠየቀ - አሰፋ ነው፡፡ አባባ ሰው እንዴት ውስጡ ዱቄት ይኖረዋል? "እኛም ውስጥ ዱቄት አለን ማለት ነው?»

ሽማግሌውም ‹‹ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ አያችሁ ልጆቼ ለሰው ውስጡ ዱቄት ስላችሁ የተፈጨን ለምግብነት የሚያገለግል ማለቴ አይደለም፡፡ ለሰው የውስጥ ዱቄት ማለት የስንዴውን ዱቄት ሰዎች እንዲመቸን አድርገን ተጠቀምንበት እንጂ ለስንዴ ዱቄቱ ዘላለማዊ እንዲሆን፣ ዘሩን እንዲያስቀጥል ማለትም ከአፋር፣ ውሃ፣ የፀሐይ ብርሃን፣ አየር በተሟሉለት ጊዜ በቅሎ፣ አሽቶ፣ ሌላ ብዙ ስንዴ እንዲሆን ተፈጥሮ ሲያመቻቸው ውስጡ ባለው ዱቄት ዘላለማዊ እንዲሆን የሚያስችሉትን ቅመሞች ሁሉ አለው፡፡ ለሰውም ሌሎችን ያለ ቅድመ ሁኔታ መውደድ፣ ተስፋ ማድረግ፣ በነፃነት ማሰብ፣ ራሱን እና ተፈጥሮን መመርመር፣ ስለቀጣይነት ማሰብ እና የራስን አበርክቶ ማበርከት ወዘተ በውስጥ ያሉ ዱቄቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሲጎሉት ግን በነቀዙ እንዳተባለው ስንዴ ቀፎው ቢኖርም ዱቄቱ የለምና ሞቷል ማለት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም መሞት ገራገር ትርጉሙ ለዘላለም መለየት ቢሆንም ለማህበረሰቡ እና ለራሳቸው አንድ ነገር የማያደርጉትም ቀፏቸው ቢኖርም በተግባራቸው አልተገለጡምና ቀድመው መሞታቸውን ያወጁ ናቸው፡፡"

> ለሰውም ሌሎችን ያለ ቅድመ ሁኔታ መውደድ፣ ተስፋ ማድረግ፣ በነፃነት ማሰብ፣ ራሱን እና ተፈጥሮን መመርመር፣ ስለቀጣይነት ማሰብ እና የራስን አበርክቶ ማበርከት ወዘተ በውስጥ ያሉ ዱቄቶች ናቸው፡፡

ሽማግሌው ስለሞት ያወሩላቸው ለልጆች እንዳልገባቸው ስለገመቱ ኃሳባቸውን ቀይረው እንደተለመደው ተረት ሊያወሩላቸው ወደዱ፡፡ "ልጆች ዛሬ የምነግራችሁ ከሰዎች ጋር ለመኖርና ደስተኛ ህይወትን ለመምራት አስፈላጊ ከሆኑት ቅመሞች አንዱ ስለሆነው ፈገግታ ነው፡፡ ትንሽ ብርሃን ብዙ ጨለማን እንደምትገልፅ ሁሉ ከውስጥ የመነጨ ፈገግታም የሀዘንን ጥላ የመግፈፍ ሀይል አለው፡፡ የሀገራችን ተረትስ «ከፍትፍቱ ፊቱ» ይባላል፡፡ ደግሞ የሚገርማችሁ ልጆች ፈገግታ እንደ ሰደድ እሳት በፍጥነት በመዛመት ከአንዳችን ወደ አንዳችን የሚተላለፍ መሆኑ ነው፡፡

እናማ ልጆች! ከሰዎች ጋር ስትኖሩ በእናንተ ምክንያት ሰዎችን ደስተኛ ማድረግ ይኖርባችኋል፡፡ ለዚህም ከፍቅር የመነጨ ፈገግታ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከሰዎች ጋር ለመኖርና በፍቅር ለማሸነፍ ፈገግታን ያህል መሣሪያ እንጂ ጉልበት እንዳይደለ የጥንት ተረት ልንገራችሁ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፤ በአለማችን ያሉ ሁለቱ ግዙፍ ሀይላት ማለትም ፀሐይና ንፋስ ‹እኔ ነኝ ሀይል› ‹እኔ ነኝ አሸናፊ› በሚለው ሀሳብ አድካሚ ክርክር ያካሂዳሉ፡፡ እንደሚታወቀው ንፋስ ፈጣን ነው እና ‹እኔ የዓለም ሁሉ አድራጊ ፈጣሪ ለመሆን የሚያስችል አቅም አለኝ፡፡ ስለዚህ ፀሐይ ሆይ! ከእኔ ጋር በትዕቢት ተወጥረሽ መከራከርሽ አቅምሽን ካለማወቅ የመነጨ በመሆኑ ክርክርሽን አቁሚና ያን ኮት ለብሶ ከምዕራብ አቅጣጫ የሚመጣውን ሰው ኮት በማስወለቅ ማን ሀያል እንደሆነ እናረጋግጥ" ፀሐይም በሀሳቡ መስማማቷን ገለፀች፡፡ ነፋስም ሀያልነቱን ለማስመስከር ሰውየውን ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከፊት ወደ ኋላ ማላጋት ሲጀምር ሰውየውም ምኑ ሞኝ ነው ኮቱን ወደፊቱ በሁለት እጆቹ ወደፊት ወጥሮ ይዞ ጉዞውን ይቀጥላል፡፡ ንፋስም ሰውየውን ማስወለቅ ባለመቻሉ ተስፋ ቆርጦ ለፀሐይ ተራውን ለቀቀ፡፡ ፀሐይ በተራዋ ምትሀታዊ የሆነ ፈገግታዋን ስትረጭበት ያው በራሱ ፈቃድ ኮቱን አውልቆ በትከሻው በመያዝ ጉዞውን ቀጠለ፡፡ እና ልጆች ከንፋስ ሀይል ይልቅ የፀሐይ ፈገግታ ተፈላጊውን ውጤት እንዳመጣ ሁሉ ከጉልበት ይልቅ ከውስጥ የመነጨ ፈገግታ የሰዎችን የአዕምሮ በር የማስከፈት አቅም አለው፡፡ ይህም ማለት ሰዎችን አስፈራርተን የምንፈልገውን ብናሰራቸው እንኳን ውስጣቸው በአመፅ መሞላቱን፣ በቂም መመረዙን አይተውም፡፡ ይህ ደግሞ ቆይቶ ተጠራቅሞ የፈነዳ እለት በቀል ሆኖ ከተፍ ይላል፡፡ ስለዚህ ከውስጥ የመነጨ ፈገግታ ጤናማ ግንኙነት እንዲኖረንና የምንፈልገውን በፍቅር በማግኘት ደስተኛ ህይወትን ለመምራት እጅግ አስፈላጊ ቅመም ነው፡፡"

ሽማግሌው ዮሴፍ ተረቱን መጨረሳቸውን ለማሳወቅ እና ምን ያህል እንደሚከታተሏቸው ለማጤን ዙሪያውን ሲያማትሩ ድምፃቸውን ለመስማት በሚያስችል ርቀት አይተዋት የማያውቋትን አንዲት ወጣት በተመስጦ ስታዳምጣቸው አይተው እንደ ጥዋት ጮራ በሚማርክ ፈገግታ ተመለከተው ወደ እሳቸው እንድትቀርብ በትህትና ጋበዟት፡፡ ለሰከንዶች በዝምታ ውስጥ ተወያዩ፡፡ ሽማግሌው ዮሴፍ የዝምታውን ብርድ ልብስ በመግፈፍ ‹‹የኔ ልጅ ስለአንች የፈለግሽውን ያህል ብትነግሪኝ መልካም ፈቃድሽ ቢሆን›› በማለት የእድሜ ብዛት ባሟሟቸው ጥቃቅን አይኖቻቸው ውስጥ ዘልቆ በሚመረምር እይታ እያዩ ጠየቋት፡፡ ‹‹አባ እኔ ብዙ ቀን በዚህ ስታልፍ ህፃናት «ጋሼ ዮሴፍ» እያሉ ሲጠሩህ ስለምሰማ ፍቀድልኝና ጋሼ ዮሴፍ እያልኩ እጠራሀለሁ፡፡ ስሜ ማህሌት የሀያ ሰባት ዓመት ሴት ነኝ፡፡ የሀገራችን መናገሻ በሆነችው አዲስ አበባ እሪ በከንቱ ሰፈር ምንም አይነት ቋሚ የገቢ ምንጭ ከሌላት እናቴ ሶስተኛ ልጅ በመሆን ይህችን ዓለም ተቀላቀልኩ፡፡ በውጣ ውረድ የተሞላ ታሪክ እንዳለኝ ይሰማኛል፡፡ ለእኔ ህይወት ፈቷን አዙራብኛለች፡፡ ይህን ሁሉ የምነግርህ ጋሽ ዮሴፍ በአንተ ላይ እምነት ስላለኝ ነው፡፡ ጋሼ ሳይህ የመኖር ተስፋን ታጭርብኛለህ፡፡ እናም ስለፈገግታ ስትነግረን የነበረውን ወደ እኔ እና እናቴ ህይወት ስተረጉመው ነበር፡፡ እናቴ ፈገግታን የእለት እንጀራዋን መጋገሪያ ርካሽ ነገር አድርጋ እኔም ውስጥ ፈገግታን ወንዶችን ማታለያ መረብ እንዳደርገው ከፍተኛ ተፅእኖ አድርጋለች" ሽማግሌው ዮሴፍ ጣልቃ ገብተው "የኔ ልጅ አሁን የነገርሽኝን እስኪ በበለጠ አብራሪው፡፡" ‹‹ምን መሰለህ ጋሼ ዮሴፍ እናቴ ባህላዊ መጠጦችን በመሸጥ ጠንከር ያለ ንፋስ በመጣ ቁጥር በስጋት፣ የዝናብ መጠን ሲጨምር በጐርፍ በሚያጥለቀልቁን ደሳሳ ቤት ውስጥ እንኖር ነበር፡፡ በእርግጥ ቤት ለመባል የሚያስደፍር አይደለም፡፡ ያው ‹ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል› እንዲሉ እኛ ለምደነዋል፡፡ ደንበኞቻችንም ብዙዎች ቤት አልባና ቤት አለን የሚሉትም ከእንደኛ አይነት የመጡ በመሆናቸው የምቾት ጉዳይ ችግራቸው አይደለም፡፡ ያም ሆኖ እናቴ አረቂ እየሸጠች ጠጥተው ሞቅ ማለት ሲጀምሩ የተሻለ ገንዘብ አለው ብላ ለምታስበው ጠጭ ያልተገደበ የውሸት ፈገግታ በጣም ከመጠን ያለፈ ታሳየዋለች፡፡ ወንዱም ከዚህ ሁሉ ሰው ተወዳጁና ተፈላጊው እኔ ነኝ በሚል እብሪት ልቡ ማበጥ ይጀምርና እናቴን ከፊት ከኋላ መነካካት ይጀምራል፡፡ ከዚያ በኋላማ ‹ምን ይሉኝ› የሚለው ባህላችን አፈር ይበላና ቤት ውስጥ ያለ ሰው ቤቱን ለቆ እንዲወጣ ይበረታታል፡፡ ስካሩ አልወጣ ያለም በሰፈራችን ጐረምሶች አስገዳጅነት እንዲወጣ ተደርጐ እናቴ ወደ መኝታ ታጣድፈዋለች፡፡ አንዳአንዴ የእኛን መኖር ይረሱትና ተጣድፈው መብራቱን ሲያጠፉት "ሳንተኛ፣ እራት ሳትሰጭን ስንል "ሰው ከእንግዳ ጋር ማረፍ አይችልም! ምናለ ቀስ ብትሉ፣ መረጋጋት ቢለምድባችሁ?" ትለናለች መጣደፏ ያመጣባትን ሀፍረት ለመደበቅ በቁጣ ስሜት፡፡

**ይቀጥላል!**

# ስብሰባው …

ከገጽ 11 የዞረ

ጥሩ ነው የሚል አስተያየት አለኝ ምክንያቱም እኔ በበኩሌ ማታ መጠጥ ነገር ቀማምሼ ስላደረኩኝ አሁን ጨጓራዬ እያቃጠለኝ ነው፡፡ ሌላው መናገር የምፈልገው ሁልጊዜ በስብሰባ ላይ የሚቀርብልን ቆሎ እየሰለቸን ስለሆነ እንዲያው እባካችሁ የሚቻል ከሆነ በለስላሳ ኩኪሶች ብትቀይሩልን… አዎ ምን አለበት መስሪያ ቤቱ ጥሩ በጀት አለው እውነቴን ነው፡፡ እኔ ለምሳሌ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ሁለት ጥርሶቼ ተነቃንቀው ስላስወለኳቸው ይኸውና እንደልቤ ቆሎ መቆርጠም አልችልም፡፡ ምን አልባት እንዲህ ያለ ችግር ያለባቸው ሌሎች የመስሪያ ቤታችን ሠራተኞች ሊኖሩ ስለሚችሉ ችግሩ እንዲታሰብበት በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡›› ብሎ ሲጨርስ ተሰብሰቢው በሳቅና በጭብጨባ አጀበው፡፡ በርካታ የመናገር እድል ይሰጠን የሚሉ እጆች ይታያሉ፡፡ አንድ በጎልማሳ የእድሜ ክልል ውስጥ ያለ ሰው እድል አገኘ ሰውየው መነጋገሪያው እጁ እንደገባ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ቆመ ‹‹ይቅርታ ወገኖቼ እኔ በስብሰባ ጊዜ ተቀምጦ የመናገር ልምድ ስለሌለኝ ነው የቆምኩት እንግዲህ ምን ማለት ነው … አዎ ከስሜ እጀምራለሁ … ስሜ ያገርሰው ታደገ ይባላል፡፡ እዚህ መስሪያ ቤት ከተቀጠርኩ ሰለቸኝ ደከመኝ ሳልል ላለፉት ሃያ አመታት ስሠራ ቆይቻለሁ ያልሰራሁበት የሥራ ክፍል የለም፡፡ ከዘበኛ እስከ አትክልተኛ፣ ከሁለገብ እስከ ውሎ ገብ ሰርቻለሁ፡፡ የዛሬን አያድርገውና እርሰዎ አቶ መልሰው የዛሬው የስብሰባ መሪያችንና የመስሪያ ቤቱ ጠቅላላ ኃላፊ ትዝ ይልዎት እንደሁ የዛሬ 12 ዓመት ገደማ እዚህ መስሪያ ቤት በጥበቃ ሥራ ሲጀምሩ … አዎ ያኔ እኔ ነበርኩ አጠቃላይ የግቢውን ሁኔታ እንዲያውቁት ዞሬ ያሳየሆት … እርሶ ጎበዝ ስለሆኑ ትምህርቶዎትን ጎን ለጎን ተምረው ስላሻሻሉ ይኸውና ዛሬ ለዚህ ወግ ማዕረግ በቁ በእውነቱ እግዚአብሔር እረዳዎት፡፡ ተመስገን ማለት ይገበወታል፡፡ ወገኖቼ ሰው መቸም አንተ ታዲያ ለምን እራስህን በትምህርት አሻሽለህ ለተሻለ የሥራ ሀላፊነት አልበቃህም ሊሉኝ ይችላሉ፡፡ አትፍረዱብኝ ወገኖቼ እዚህ መስሪያ ቤት ከመቀጠሬ በፊት ብዙ ልጆች ወልጄ ስለነበር ለመማር አልቻልኩም፡፡ በእርግጥ መድህኒያለም ምስጋና ይግባውና ተጎትቶም ቢሆን ያሳደኳቸው ልጆቼ ለቁም ነገር እየበቁልኝ ነው›› እያለ ሲቀጥል ተሰብሳቢው የማጉረምረም ድምፅ በማሰማቱ አቶ ያገር ሰው እባክህ ወደ ዋናው አጀንዳ ግባ ጊዜያችንን በአግባቡ እንጠቀምበት በተነሱት እርዕሶች ላይ ብቻ ሃሳብህን ቀጥል ›› አሉት- ሰብሳቢው፡፡ ‹‹ይቅርታ›› አለና ቀጠለ-ተናጋሪው ‹‹ምን ለማለት ፈልጌ ነው ዛሬ የእረፍት ቀኔ ነበር ስብሰባው የውሎ አበል አለው የሚል ወሬ ሰምቼ ነው የመጣሁት በእውነቱ ዛሬ በዚህ ስብሰባ ላይ በመገኘቴ ደስተኛ ነኝ፡፡ አመሰግናለሁ ›› ብሎ ተቀመጠ፡፡ መጠነኛ ጭብጨባ ከተሰብሳቢው ተሰማለት፡፡

ስብሰባው ቀጥሏል፡፡ ስብሰባው ይጠቃለላል የተባለበት ሰዓት ሊያበቃ የተወሰኑ ደቂቃዎች ቀርተዋል፡፡ አንድ ሰው መናገር ጀመረ ‹‹ስለተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ ስሜን መናገሩ አይጠቅምም ዋናው ሃሳቤ ነውና የሚያስፈልገው በቀጥታ ልናገር ወደምፈልገው ጉዳይ እገባለሁ አዎ ካስፈለገም ደግሞ ስሜን እናገራሁ ስሜ ደፋሩ ሽመክት ይባላል፡፡ እ … እ.. እ… እኔ የሚገርመኝ ቢኖር የስብሰባ ጉዳይ ነው፡፡ ሀገር በስብሰባ ታድግ ይመስል ነጋ ጠባ ስብሰባ ነው፡፡ ይኸ መንግስትማ አበዛው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ሀገር በሥራ እንጂ በስብሰባ አታድግም ፡፡ በስብሰባ ብዛት ያደገች ሀገር በታሪክ አልሰማንም አላየንም ወገኖቼ ስሙኝማ አንዲት ሀገር በስብሰባ የምታድግ ቢሆን ኖሮ እ… ድህነት በስብሰባ ብዛት የሚጠፋ ቢሆን ኖሮ ይህች የእኛ ሀገር ኢትዮጵያችን እስከ አሁን አውሮጳንና ኢሲያን በልጣ ትገኝ ነበር፡፡ እስቲ እናስብ ወገኖቼ ከንጉሱ ዘመን ጀምሮ በደርግ ጊዜም ብዙ ስብሰባዎች ተደርገዋል በተለይ በተለይ በዚህ መንግስትማ በዛ … ኧረ በዛ … በቴሌቮዥንና በራዲዮ የምንሰማው ዜና የስብሰባ ነው፡፡ ምነው ጎዝ ሥራ ቢሠራ ሀገር በስብሰባ ዜና አትለወለጥም … ›› እያለ ሲናገር አጠገቡ የተቀመጠው ጓደኛው ነካ ሲያደርገው መናገሩን አቁሞ ወደ ጓደኛው ዘወር አለ ጓደኛውም ወደ ጆሮው ጠጋ ብሎ በቀስታ ድምፅ ‹‹ምንነካህ ደፋሩ የምትናገረውን እያስተዋልክ ነው? ፖለቲካ ነው እኮ ›› ሲለው ደፋሩ እንደ መደንገጥ ብሎ… ንግግሩን ቀጠለ በግንባሩ አካባቢ ላብ ነገር ችፍፍ ብሎ ይታያል፡፡ ድምፁ የፍራት ስሜት እንደተፈጠረበት ያሳብቅበታል፡፡ ቀጠለ ደፋሩ፣ ይቅርታ ወገኖቼ ትንሽ ስናገር ስሜታዊነት ይታይብኛል፡፡ እኔ ፖለቲካ አልወድም፡፡ ‘ፖለቲካንና ኤሌክትሪክን በሩቁ’ ሲሉ እሰማ ነበር ኢህአፓዎች አዎ መቼም ‘የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም’ ነውና የሚባለው… እስካሁን መንግስት እያልኩ የተናገርኩት ቃል መስሪያ ቤታችን በሚለው ይስተካከልልኝ… ክቡር ሰብሳቢያችን… አዎ ስብሰባ በጣም ጠቃሚ ነው እንዲያውም በዚህ አጋጣሚ አንድ ግጥም እንዳሰማ ይፈቀድልኝ አለና ፍቃድ ሳይሰጠው ቀጠለ፡፡ ግጥሟን የምላት በቃሌ ነው የግጥሟ ርዕስ «ስብሰባ» የምትል ናት፡፡

ስብሰባ ጥሩ ነው ለአፍሪካ

የሰዎችን መብት ሳይነካ

ስብሰባ ጥሩ ነው ለኢትዮጵያ ሀገሬ

ታዲያ ለምን? ተወደደ ሽሮና በርበሬ… አመሰግናለሁ…» ብሎ ሲጨርስ አዳራሹን ሳቅና ጭብጨባ አደመቀው፡፡ በመድረኩ ላይ የተሰየሙት ሰብሳቢዎችና ጋዜጠኞችም ሳቅ እንደተፈታተናቸው ያስታውቅ ነበር፡፡ ሳቅና ጭብጨባው ጋብ እንዳለ ሰብሳቢው መነጋገሪያውን በመዳፋቸው መታ መታ አድርገው «ውድ ተሰብሳቢዎቻችን… አንድ ጊዜ እንደማመጥ… እባካችሁ ወደ ዋናው እርዕሳችን ገብተን ብንነጋገር መልካም ነው፡፡ አንዳንዶቻችሁ የስብሰባ አጀንዳችን ለማስቀየስ የምታደርጉት ጥረት ጥሩ አይደለም፡፡ ለማንኛውም ይህንንም ጉዳይ ቢሆን በኋላ በስብሰባችን ላይ የምናየው ይሆናል፡፡ አሁን እድሉን ለተሰብሳቢው እሰጣለሁ፡፡» አሉ ኃላፊው፡፡

ስብሰባው ቀጥሏል፡፡ አሁን አንዲት በእድሜአቸው ጠና ያሉ ሴት እጃቸውን ሲያውለበልቡ በሰብሳቢው እይታ ውስጥ ገቡ፡፡ «እሺ… እዚያ ጋ ሴቶች ተሳትፎአቸውን እናበረታታለን፡፡» አሉና እድሉን ሰጡ ሴትዮዋም መነጋገሪያውን እንደተቀበሉ ከመቀመጫቸው በመነሳት ቆመው መናገር ጀመሩ… «እሺ ለተሰጠኝ እድል በቅድሚያ ኃላፊያችንን አቶ መልሰውን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ በመቀጠል ከእርሳቸው ጐን ሆነው ቃለ ጉባኤ የሚይዙትን ሰውና እንዲሁም ሶስተኛውን ወንድማችንን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ መቼም በዚህ መስሪያ ቤት እኔን የማያውቅ ሰው ያለ አይመስለኝም፡፡ ለማንኛውም ትናንት ተቀጥሮ ዛሬ ለስብሰባ የመጣ ሊኖር ስለሚችል እንደሚከተለው ስሜን አስተዋውቃለሁ… እንግዲህ ምንድነው እሱ ስሜ ወ/ሮ ወርቅ ያጥፍ ቼሬ፣ ቸሬ ጓንጉል፣ ጓንጉል መካሻ እባላለሁ፡፡ አዎ እኛ ዘረ ብዙዎች ነን ያውም የባላባቶች ትውልድ ነፍሳቸውን ይማርና…» በማለት ሊቀጥሉ ሲሉ ሰብሳቢው ጣልቃ ገብተው «ይቅርታ ወ/ሮ ወርቅያጥፉ… እራስዎትን ማስተዋወቁ ይበቃናል… ወደ ዋናው የስብሰባ ሀሳብ ይግቡ» አሏቸው፡፡ «እሺ ክቡር ሰብሳቢ ምንድነው እሱ እኔ መናገር የምፈልገው እንደሚታወቀው ዛሬ አቡዬ ናቸው ጠዋት አመጣጤ ፊርማ ፈርሜ ወ/ሮ ጌጤ ጠበል ቅመሱ ጥሪ ስላለባት ሥራ አግዛታለሁ ብዬ ወደ ቤቴ ለመመለስ ነበር፡፡ ከስብሰባው መቅረት የለብሽም ስላሉኝ ከጓደኛዬ ከወ/ሮ ማዘንጊያሽ ጋር ተያይዘን መጣን፡፡ እና ምንድን ነው አሁን መናገር የምፈልገው፡፡ ይኸ ተሰብሳቢ ማወቅ ያለበት ጉዳይ ቢኖር፣ እዚህ መስሪያ ቤት የመልካም አስተዳደር ችግር አለ፡፡ አዎ… ባለፈ የዚህ መስሪያ ቤት ባልደረባ የሆነችው ወ/ሮ ተዋበች አጐቷን ተረድታ ሀዘን ተቀምጣለችና ለቅሶ ድረሱ ብለን በማስታወቂያ ቦርድ ላይ ለጥፈን ነበር፤ ነገር ግን የመጣው ሰው በጣም ጥቂት ነው፡፡ በቀደም ደግሞ የአቶ መላኩ ቤት የጊዎርጊስ ጠበል ቅመሱ ብለን ማስታወቂያ ለጥፈን እግዜር ያሳያችሁ የመጣው ሰው ያልተጠራው ሁሉ ነው፡፡ ይኸ ታዲያ ምንድነው? ማዳላት አይደለም? የመልካም አስተዳደር ችግር አይደለም? ስራን ጥሎ ለሆድ መሯሯጥ ማለት አይደለም፡፡ ጨርሻለሁ፡፡ አሉና ተቀመጡ፡፡ ተሰብሳቢው አጨበጨበ፡፡ በርካታ እጆች ሲውለበለቡ ይታያሉ፡፡ “ጎበዝ በዋናው የስብሰባ አጀንዳዎቻችን ላይ ሀሳባችሁን ብታቀርቡ ጥሩ ነው፡፡›› አሉና ሰብሳቢው ሌላ እድል ሰጡ፡፡ ይኸ ወጣት ነው ፡፡ መነጋገሪያውን ተቀብሎ መናገር ጀመረ፡፡ ‹‹ኦኬ ለተሰጠኝ ቻንስ ታንኪው ብያለሁ፤ ዌል… እኔ መናገር የምፈልገው ስለ መስሪያ ቤቱ ቪዥን ኤንድ ሚሽን ነው፡፡ አይነው ማንጅመንቱ እንዴት እንዳየው አላወቅም በዋናው በር የቆመው ታፔላ ኦልድ ከመሆኑ የተነሳ አንዳንድ ሌተሮች ጠፍተዋል፡፡ በዚህ ምክንያት በግልጥ አይታይም ሚኒንጉ የተዛባ ሆኗል፡፡ እንደእኔ እንደእኔ ፎከስ ቢደረግበት አሪፍ ይመስለኛል፡፡ ለዚህ ሥራ ደግሞ መስሪያ ቤቱን ለመተባበር በበኩሌ ሬዲ ነኝ፡፡ እንደውም በዚህ ሞያ የሚሠራ አንድ ፍሬንድ ስላለኝ ከመስሪያ ቤቱ ጋር እርሌሽን እንዲፈጥርና እሱ እንዲሠራው ለማድረግ እችላለሁ በድጋሜ ለተሰጠኝ ቻንስ ታንኪው›› ብሎ አበቃ፡፡ አሁንም «እዚህ እዚህ» የሚሉ የእጅ ምልክቶችና ድምፆች ይሰማሉ በዚህ ሁኔታ ላይ ከጋዜጠኞቹ መካከል አንዱ ወደ ሰብሳቢው ተጠግቶ የሆነ ነገር በጆርአቸው ተናገራቸው፡፡ ‹‹እሺ ይበቃናል›› አሉ ሰብሳቢው፡፡ «አሁን ሰዓቱ ስለደረሰና ጋዜጠኞቻችንም ሊሄዱ ስለሆነ የዛሬውን ስብሰባችንን በዚሁ ላይ እናበቃለን ጥሩ ጥሩ ሀሳቦች ከተሰብሳቢው ተነስተዋል፡፡ ለተነሱት ሃሳቦች በጣም እያመሰገንናችሁ እነዚህን ሃሳቦች በማዳበር ወደፊት ተቋማችን የተሰጠውን የህዝብና የመንግስት ልማታዊ አደራ እንደምንወጣ ቃል እንገባለን የሥራ አመራር አካሉም ይኸንን ትኩረት ሰጥቶ እንደግብዓት ተጠቅሞ እቅዶችን ስለሚያወጣ በድጋሜ ለተሰጡት ሀሳቦች በራሴና በሥራ ኃላፊዎች ስም አመሰግናለሁ›› ሲሉ አዳራሹ በጭብጨባ ደመቀ፡፡ የእለቱ ስብሰባም በዚህ ተጠናቀቀ፡፡

* * *

ዏዏዏዏዏ

# እንግዳችን

ከገጽ 9 የዞረ

**ናይል፡- በቅርቡ በኬንያ (Univresity of Kanyata) አለም አቀፍ ጉባዔ ላይ ተጋብዘው ነበር፡፡ ስመሆኑ ጉባዔው በምን ጉዳይ ላይ የተዘጋጀ ነበር? እርስዎ የነበረዎት ሚና ምን ነበር?**

*ዶ/ር ዓለማየሁ፡- ኬንያታ ዩኒቨርሲቲ "ድህረ 2015 የልማት አጀንዳ - ትምህርትን ወደ ፊት ማንቀሳቀስ" በሚል ሁለተኛውን አለም አቀፍ የትምህርት ኮንፍረንስ በፈረንጆች አቆጣጠር ከጥቅምት 8th -9th /2015 አዘጋጅቶ ነበር፡፡ በዚህ አለም አቀፍ የትምህርት ኮንፍረስ ዋና የክብር እንግዳ፣ (Chief Guest ad keynote speaker) በመሆን ከመጋበዜ በተጨማሪ "The Impact of Education on Rural Women's Participation in Political and Economic Activities" በሚል ራዕይ የምርምር ውጤት አቅርቤአለሁ፡፡ በዚህም ሰርቲፍኬት የምስጋና ደብዳቤ እና ሽልማት ተቀብያለሁ፡፡*

*በኮንፍረንሱ ከተለያዩ የአውሮፓ፣ የእስያ እና የአፍሪካ አገራት ፕሮፌሰሮች የምርምር ውጤታቸውን አቅርበዋል፡፡ ይህም ከተለይዩ አገሮች ከመጡ ፕሮፌሰሮች ጋር እንድተዋወቅ ዕድል ፈጥሮልኛል፡፡*

**ናይል፡- ሴሎች ምሁራንና ተመራማሪዎች በእንዲህ ዓይነቱ ዓለም አቀፍ ጉባዔ ተሳታፊ ይሆኑ ዘንድ ምን ይመክራሉ?**

*ዶ/ር ዓለማየሁ፡- በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአምስት አመት ስትራቴጅክ ዕቅድ ውስጥ ትኩረት ከተሠጣቸው ተግባራት ውስጥ የዩኒቨርሲቲውን መምህራንና ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ማዳበር ነው፡ ፡ ይህንንም በተግባር ለመተርጎም መምህራንና ተማሪዎች የምርምር ሥራዎቻቸውን በተለያዩ አለም ዓቀፍ ኮንፍረንስ ለማቅረብ ዕድሉን ካገኙ ዩኒቨርሲቲው ሙሉ ወጪአቸውን ሸፍኖ ለመላክ የሚያስችል የማበረታቻ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶል፡፡ በቦርድ መፅደቅ ብቻ ይቀረዋል፡፡ ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያካበቱትን የምርምር ልምድ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለማስፋፋት ያስችላል ተብሎ ታምኖበት ነው፡፡ ይህንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መምህራንና ተማሪዎች የምርምር ሥራዎቻቸውን በታዋቂ አለም አቀፍ ኮንፍረንስ ለማቅረብ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ በርካታ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለምሳሌ፡- እኔ ኬንያታ ዩኒቨርሲቲ ሄጀ የምርምር ሥራ በማቅረቤ በረካታ የአፍሪካ አገራት ጥሪ ቀርቦልኛል፡፡ ይህም በሰለጠንሁበት የሙያ መስክ ከተለያዩ አለም አገራት ከመጡ ባለሙያዎች ጋር ለመተዋወቅና ትስስር ለመፍጠር ይረዳል፡፡*

**ናይል፡- ማስተሳሰፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካስ እድሉን ልስጥዎት፡፡**

*ዶ/ር ዓለማየሁ፡- የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ራዕይውን ለሁሉም ማህበረሰብ በሚገባ ግንዛቤ ፈጥሯል፡፡ ቀጣዩ ሁሉም የበኩሉን ድረሻ እንዲወጣ አመራሩ የማስፈፀሚያ ሥልቶችን በመቅረፅ ለአተገባበሩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡ የምንከተለው ሥልት (Open The Door and Furnish the Room) መርህ ነው፡፡ ይህ ማለት ራዕይውን ለማሳካት አልጋ በአልጋ ይሆናል የሚል እምነት የለኝም፡፡ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ማለትም የሰው ኃይልና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ የአሠራር፤ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓቶች በሙሉ ተሟልቷል የሚል ዕምነትም የለኝም፡፡ ነገር ግን ባለን ውስን አቅም፤ ባሉን ውስን ምርጥ ባለሙያዎች እና ለመነሻነት የሚያገለግሉ መሳሪያዎች በመጠቀም የኛን ቁርጠኝነትና፣ ታታሪነት በማከል የምንፈልገው ግብ መድረስ እንደምንችል አምነን ሁላችንም ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ዕድገት የበኩላችንን ድርሻ እንድንወጣ ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡*

**ናይል፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን!**

*ዶ/ር ዓለማየሁ፡- እኔም አመሰግናለሁ!*

## ለመጀመሪያ ዓመት ሴት

... ከገጽ 4 የዞረ

ማስወገድ እንዳለባቸው፣ በዕቅድ የመመራት ባህልን ማዳበር፣ የጊዜ አጠቃቀም፣ በጾታ ትንኮሳ ምንነት ማወቅና እንዴት ማስወገድ እንደሚችሉ፣ የቡድን ሥራንና የመረዳዳት ባህልን ማዳበር፤ ውጤታማ የሆነ የማንበብ፣ የማስታወሻ አያያዝ፣ በክፍል ውስጥ የማቅረብ እንዲሁም የፈተና አወሳሰድና ተሳታፊ መሆን በሚሉ ርዕሶች ዙሪያ በቂ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡

የስልጠናው ተሳታፊ የሆኑት ተማሪ ነብያት እና ተማሪ ሶፊያ ለሁለት ቀን የተሰጣቸው ስልጠና ለህይወታቸው በጣም ጠቃሚ እንደሆነና በዩኒቨርስቲ ቆይታቸው ወቅት የሚገጥማቸውን ችግር እንዴት ማስወገድ እንደሚችሉ መንገድ ያሳየ ስልጠና እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ሌሎችም ክፍሎች እንዲዚህ አይነት መርኃ ግብር አዘጋጅተው ለተማሪዎቻቸው ልምድ ቢያካፍሉና አዲስ ሴት ተማሪዎችን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

## በተማሪዎች የተሰሩ...

ከገጽ 4 የዞረ

ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ የሚያገለግል ማሽን፣ ሰው አልባ ጀልባ፣ ወደ ጠፈር ከሄደ ተመራማሪ ጋር የሚያገናኝ የሚችል እና የቋንቋ ማስተማሪያ የሚሆን ሶፍትዌር፣ በፀሀይ የሚሰራ መኪና፣ አምፖል፣ ዳቦ መጋገሪያ፣ የትራፊክ መብራት፣ ማቀዝቀዣ ማሽን፣ የውሃ ማሞቂያ እንዲሁም በማዕከሉ ዙሪያ የተተከሉ የተለያዩ የአትክልትና የሰብል አይነቶች ተማሪዎቹ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ በየጊዜው እየተከታተሉና እየተንከባከቡ የሚያገኙትን ለውጥ ትንታኔ የሚሰጡበት የግብርና ሥራ የሚካሄድበት ቦታ ተጎብኝቷል፡፡

ተማሪዎቹ የቤተ ሙከራ ውስጥ ፕሮጀክት በመቅረፅ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ቁሳቁሶች ከ10 በላይ የፈጠራ ሥራዎችን ለመሥራት የተወዳደሩ ሲሆን ከ1ኛ እስከ 3ኛ ደረጃ ለወጡ ተማሪዎች የሳምሰንግ ጋላክስ ታብሌት፣ የስማርት ፎን እና የአይ ፓድ ሽልማት ከዩኒቨርሲቲው ተበርክቶላቸዋል፡፡ በተጨማሪም በማዕከሉ ከታቀፉት ተማሪዎች መካከል በማዕከሉ ውስጥ ሰፊ ጊዜን በማሳለፍ አርአያ ለሆኑ ተማሪዎችም ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ደረጃ ተሰጧቸው ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡

ሽልማት ካገኙት ተማሪዎች መካከል የ11ኛ ክፍል ተማሪ አሸናፊ ይመኝ እና የ12ኛ ክፍል ተማሪ ናሆም ደበበ በሁለት አይነት የፈጠራ ሥራዎቻቸው ብቸኛ የሁለት ጊዜ ተሸላሚዎች ሲሆኑ ዩኒቨርሲቲው እያደረገ ያለውን ድጋፍ በማድነቅ ሽልማቱም ወደፊት የበለጠ እንድንጥርና እንድንሰራ እንዲሁም ከፍተኛ ኃላፊነት እንድንሸከም የሚያደርገን ነው ብለዋል፡ ፡ ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው ከሚገኙ የወዳደቁ ቁሳቁሶች የፈጠራ ሥራዎች መስራታቸው የሳይንስ ፈጠራዎችን በቀላሉ የሚማሩበትና የሚለማመዱበት አጋጣሚ እንደፈጠረላቸው ተናግረዋል፡፡

ማዕከሉ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እና ሚስተር ማርክ ጌልፈንድ ፋሚሊ ትረስት በተባለ ድርጅት ድጋፍ የተቋቋመ ሲሆን ከ7ኛ-12ኛ ክፍል ያሉ በሳይንስ ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ከ500 በላይ ተማሪዎችን በመምረጥ በየዓመቱ በክረምቱ የእረፍት ጊዜያቸው የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግና ሂሳብን በቀላል ዘዴ ሳይሰላቹ እንዲማሩ በማድረግና አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችን ለመፍጠር በሚያመች ዘዴ እያሰለጠነ ይገኛል፡፡

## የዘር ብዜት ስርጭት ...

ከገጽ 4 የዞረ

የተቀናጀ የዘር ብዜትና ግብይት ፕሮግራም የሚያከናውናቸው ተግባራት አርሶ አደሮችን በማደራጀት የዘር ብዜትና ግብይት ላይ እንዲሠሩ በማህበር ማደራጀትና ማጠናከር፣ የግል ዘር አምራች ድርጅቶችን ማስፋፋትና ማጠናከር፣ የተለያዩ አጋር ድርጅቶች በዘር ልማት ዘርፍ ረገድ የሚያግዙ የፈጠራ ሥራዎችና የተገኙ ግኝቶች ላይ ድጋፍ በማድረግ የዘር ነክ ማነቆዎችን ለመፍታት በሚደረገው እንቅስቃሴ በመሳተፍና ምርታማነት በማጠናከር የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ ከማድረግ ባለፈ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ እድገት የበኩሉን ሚና እየተወጣ እንደሚገኝ በውይይቱ ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የዘር ብዜት ማህበራቱ የሚያጋጥማቸውን ተግዳሮቶች ለመፍታት አጋር ድርጅቶች በጋራ በመንቀሳቀስ እነዚህ ማህበራት ጠንካራ ኢኮኖሚ እንዲኖራቸው በማገዝ ለአርሶ አደሩ የሚፈልገውን ያህል የተሻሻለ ዘር እንዲያገኝ ማገዝ እንደሚኖርባችውና የክልሉን የዘር ዘርፍ ጥራት ለማሻሻል በዘር ሰንሰለቱ ያለውን ተግዳሮት ተመራማሪዎች ከምንጩ በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በውይይት መድረኩ የዘር ብዜትንና ስርጭትን በተመለከተ ያጋጠሙ መልካም አጋጣሚዎችና ተግዳሮቶች በባለሙያዎች የተጠኑ አራት የምርምር ውጤቶች ለተሳታፊዎች የቀረበ ሲሆን በተሳታፊው የተነሱ የተለያዩ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የተቀናጀ የዘር ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (ISSD) የዩኒቨርሲቲው እና የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ከፍተኛ አመራሮች እንዲሁም በክልሉ ውስጥ በዘር ዘርፍ ላይ የሚሰሩ የሥራ ክፍሎች በተገኙበት የመስክ ምልከታ አካሄደ፡፡ የመስክ ምልከታው ዋና አላማ በ2007 ዓ.ም ፕሮጀክቱ በተለያዩ ወረዳዎች የሰራቸውን ስራዎች ምልከታ ማካሄድ፣ ለቀጣይ ስራ ሙያዊ የሆነ አስተያየት ማግኘት፣ በዘር ዘርፉ ከሚሰሩ ድርጅቶች ልምድ ማግኘት እና ልምድ መስጠት እንዲሁም የጋራ ምክክር ማካሄድ ነው፡፡

በመስክ ምልከታው ላይ የክልሉ የግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ሹምዬ አለሙ የተቀናጀ የዘር ዘርፍ ልማት ፕሮግራም በዋነኛነት የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ከማገዝ አኳያ የአንበሳውን ድርሻ ወስዶ እየሰራ መሆኑን ገልጸው ከዚህ በፊት በመንግስት ብቻ የሚቀርብ የነበረውን የዘር አቅርቦት አሁን በማህበራትና በግል ዘር አቅራቢዎች እንዲቀርብና አርሶ አደሩ አማራጭ ዘር እንዲያገኝ እያደረገ ያለ ፕሮጀክት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ ፕሮጀክቱ የዘር ብዜት ሥራን አሁን በክልሉ ውስጥ በሚገኙ 23 ወረዳዎች ላይ ዘር የማብዛት ሥራ እየሰራ እንደሚገኝና የሥራ አድማሱን ከዓመት ዓመት በማስፋት በክልሉ ላይ ጥራት ያለውና የተሻለ አቅርቦት እንዲሁም የተሻለ ግብይት እንዲኖር እየሰራ እንደሚገኝና ባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ ከአመራር እስከ ባለሙያ ያሉት አካላት ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እየሰሩ እንደሚገኙና ወደፊትም ከዚህ የበለጠ መስራት እንደሚጠበቅባቸው አቶ ሹምዬ ገልጸዋል፡፡

ፕሮጀክቱ በክልሉ ውስጥ ተማራጭና ጥራት ያለው ዘር እንዲሁም የአገሪቱን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ዋነኛ ተልዕኮ አድርጎ እየሰራ እንደሚገኝና ከመደበኛው የተሻለ የምርት አቅርቦትና ሁሉን አቀፍ የዘር ዘርፍ ልማትን በማጐልበት እየሰራ እንደሚገኝ የገለፁት የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ዶ/ር ደረጀ አያሌው ናቸው፡፡ ለማሕበራት፣ ለግል ዘር አባገሮች እንዲሁም ለዘርፍ ባለሙያዎች የስልጠና፣ የልምድ ልውውጥ፣ የገንዘብ እርዳታ፣ የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፣ ማስተዋወቅና የምርምር አገልግሎት በዋነኛነት እየሰጠ ይገኛል ብለዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ የመስክ ምልከታው አስተማሪና አበርታች እንደነበር ገልጸው ፕሮጀክቱ ሲያበቃ የሚቆም ሣይሆን በዘለቄታዊነት እንዲቀጥል ከፌደራልም ሆነ ከክልሉ መንግስት ጋር በጋራ መስራት እንደሚያስፈልግ እና የክልሉ አመራር ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ሊሰራ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲውም በምርምርና በስልጠና እንደሚያግዝና ለወደፊቱም ከጐናቸው በመቆም በጋራ እንደሚሰራ ዶ/ር ባይሌ ተናግረዋል፡፡

ከወንበርማ ወረዳ የዘር ብዜት ማህበር (ማርወለድ) እና የግል ዘር አብዥ ድርጅት (አባይ በልስቲ) እንዲሁም ከጃቢጠና ወረዳ በቀጥታ የዘር ግብይት ስርዓት የተሳታፊ የዘር ብዜት ህብረት ሥራ ማህበር (እድገት በር የዘር ብዜትና ግብይት ህብረት ሥራ ማህበር) የመስክ ምልከታው የተካሄደባቸው ማህበራት ናቸው፡ ፡ በመጨረሻም ከመስክ ምልከታው የተገኙ ጠንካራና ደካማ ጐኖችን በማንሳት የተለያዩ ውይይቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡

# The 14th International Symposium on Equatorial Aeronomy (ISEA) at BDU




















# Photo Gallery





German visitors at BDU









BDU - ISSD's field visit and discussion with Stakeholders

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የባለፈው ወር እትማችን ላይ መስከረም 2007 ዓ.ም ተብሎ የተጠቀሰው 2008 ዓ.ም ተብሎ እንዲስተካከል እንዲሁም የዶ/ር ጀማል ሙሀመድ 'መረጃና የመረጃ ምንጮች ቁማር' በተሰኘው ፅሁፍ ላይ 'ከልምድ እንደምናየው ብዙዎቹ ...ሥራን መዝጋት የሚቻልበት ገጠመኝ አድርጎ መውሰድ የተለመደ ተግባር ነው፡፡' የሚለው በስህተት የገባ መሆኑን እየገለጽን ለተፈጠረው ስህተት ፀሃፊውንና ውድ አንባቢዎቻችንን ይቅርታ እንጠይቃለን!

ጎህ ማተሚያ ቤት ታተመ